# የሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክት ወደ ኤፌሶን ሰዎች

(ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የተዘጋጀ)

**(የኢትዮጵያውያን ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤ/ክ)**

**ዳላስ**

**ቅዱሳንን የማጽናት አገልግሎት**

Ethiopian Evangelical Baptist Church

2822 S Jupiter Rd, Garland TX 75041

**www.wongelkedallas.org**
**www.eebc-dallas.org**
**Tel.2147030100**
**Fax 2147030161**

June 2012

# የኤፌሶን መልዕክት ጥናት

## መግቢያ

የመጽሐፉ መግቢያ እንደሚያመለክተን የኤፌሶን መልዕክት የተጻፈው በሐዋርያው ጳውሎስ ነው (ኤፌ 1፡1)። ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ጌታ ከመምጣቱ በፊት ከአይሁዳውያን ሸንጎ አባላት አንዱ ነበር። ደግሞም የህግ ምሁርም ነበር። ነገር ግን ከሁሉ ለሚበልጠው ለክርስቶስ ባሪያ ሆኗል። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን መልዕክት የጻፈው በኤፌሶን ለነበሩ የአይሁድና የአህዛብ አማኞች ቤ/ክ ነው። ስለ ኤፌሶ ከተማ ወንጌል የሐዋ 19-20 እና ራዕይ 2፡ማንበብ ጥሩ እውቀት ይሰጣል።

ይህች ከተማ በዛሬው ምዕራባዊ ቱርክ ትገኛለች። ወደብና ንግድም የነበራት ከተማ ነች። የንግድ ከተማም በመሆኗ ብዙ ዓይነት ህዝብ ይኖሩ ነበር። ሐዋርያ ጳውሎስ በኤፌሶን ከተማ ለነበረችው ቤተክርስቲያን ከሮም እስር ቤት በ60 ዓ/ም ገደማ እንደጻፈ ብዙዎች ይስማማሉ። በዚህ ከተማ ከሶስት ዓመት በላይ እንደቆየም ይታወቃል።

የኤፌሶን፣የቆላስይስ፣የፊልሞናና የፊልጵስዩስ መልዕክቶች በተመሳሳይ ጊዜ ከሮም እስር ቤት እንደተጻፉ ይታወቃል። የኤፌሶን ከተማ በጣኦት አምልኮ በተለይም ሮማውያን ዲያና፤ ግሪኮች አርጤምስ ብለው ለምያመልኳት ጣኦት የታወቀ ቤተ መቅደስ ነበራት (ይህም ቤ/መቅደስ በዓለም ከታወቁ ሰባት ታላላቅ ነገሮች አነዱ እነደሆነም ይነገራል)። የኤፌሶን ከተማ በጊዜው ከነበሩ ትልልቅ ከተሞች እንደ ሮም፣አንጾኪያ፣ቆሮንቶስና እስክንድርያ እንደ አንዱ ትመደባለች።

## የመልዕክቱ ዓላማ፡-

የከበረና ያልታወቀ ብልጥግና ለክርስቲያኖች ወይም ለቤተክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጥቷል (ኤፌ 1፡3-6)። ነገር ግን ብዙዎቹ በዚህ ምድራዊ ነገር ያነጻጽራሉ ይመዝኑታል እንደውም ያሳንሱታል። ሰዎች በዘር፣ በጎሳና በነገድ ልዩነት ክርስቲናን ይለውጣሉ፣ያሳንሱታልም። የሀብታም ልጅ የባለጠጋ ልጅ መሆኑና ካላወቀና በክብር ካልያዘ ምን ይጠቅመዋል። እንደዚሁም ሐዋርያው ለኤፌሶን አማኞች ማስተላለፍ የፈለገው መልዕክት የእግዚአብሔርን የዘለላም እቅድና የጸጋውን ስፋትና ጥልቀት ይበልጥ እንዲረዱና ጌታ ለቤ/ክ ያለውን ታላቅ በረከት ማድነቅ እንዲችሉ ነው። ለዚህም ችግሩ የመንፈሳዊ ዓይን ብርሃን ጉድለት ስለሆነ መንፈሳዊ ዓይን ሊበራ ይገባል። ለዚህም ጸሎት መሰረታዊ ነገር ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡን ባርኳል። ይህም ምስጢር ከምንም ጋር አይነጻጸርም።

ሌላው ድነት ለራሳችን ጥቅም ብቻ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ክብርና ውዳሴ ጭምር እንደሆነ በአጽንኦት ያሳስባል (ኤፌ 1፡6)። ክርስቲያኖች ሙሉ ጽድቅና ቅድስና ባለበት ሰማያዊ ሥፍራ እስኪቀመጡ ድረስ በምድር ላይ ባለች ቤ/ክን ጌታ በሰጣት የጸጋ ስጦታዎች እርስ በርስ እየተናነጹ ጥልቅ የክርስቶስን ፍቅር እየተካፈሉ የየዕለት ኑሮአቸውን ለጌታ ክብር እንዲኖሩ ያሳስባቸዋል (ኤፌ 1፡3)።

ይህ መልዕክት እንደሚታወቀው በጸሎት የታወቀ መልዕክት ነው። የጸሎቱም ዋናው ዓላማ ለመንፈሳዊ ዓይን ብርሃንና የጌታን ጥልቅ ፍቅር ስለማወቅ ነው። ስለዚህ እኛም ዓይናችን እንዲበራ በግልና በማህበር ጥልቅ ጸሎት መጸለይ አለብን። በተጫማሪም የመንፈሳዊ ውጊያ መርህ በቂ እውቀት ሊኖረን ይገባናል (ኤፌ 6፡10-18)።

ይህ የኤፌሶን ጥናት ሲዘጋጅ ዋናው ዓላማ ቤተክርስቲያናችን እያንዳንዳችን ይህንን የእግዚአብሔርን የድነት ጥልቅ ምስጢር እንድናውቅና እግዚአብሔርን እንድናወድስ በተጨማሪም ለበለጠ ብርሃን እንድንዘጋጅ ነው። ሁላችንም ለዚህ መገለጥና ጥበብ እንጸልይ መንፈሳዊ ውጊይም በየቀኑ እናድርግ። ቅዱሳንን የማጽናት አገልግሎት

# ጥናት አንድ

የምንባብ ክፍል **ኤፌ 1፡1-14**

ሁሉ ክብሩ ለእግዚአብሔር ይሆን ዘንድ ነው

## ዓላማ፡ -

እግዚአብሔር እኛን በመጥራቱ እና በማዳኑ ውስጥ ያደረጋቸው ነገሮች በሙሉ በስ ተመጨረሻ ለሰው ልጆች ድነት እና ለእርሱ ለራሱ ክብር እንዲሆን መሆኑን በማስተዋል፣ በተዋጀው ሁለተናችን የምናደርገው ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር መሆን እንዳለበት ማሳሰብ

## መግቢያ፡-

ብዙ ጊዜ ስለ መጠራታችን እንዲሁም በድነታችን ስላተረፍነው መልካም ነገር ስናስብ ምን ያህል ዕድለኞች እንደሆንን እንቆጥራለን። በእርግጥም፣ በታላቁ በእግዚአብሔር ዘንድ መታሰብ እና ክርስቶስ ለእኛ ይሞት ዘንድ መምጣቱ ከአዕምሮ በላይ ነው። ሆኖም ግን ወደ ኤፌሶን መጽሐፍ መጥተን፣ የእግዚአብሔርን ቃል ስናጠና፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ሲዋጀን እኛን ከማክበሩ በላይ ሌላ ታላቅ አላማ እንዳለው ያሳየናል። ያም የእግዚአብሔር ዓላማ በሁሉ ነገር መጨረሻ ክብሩ ለእርሱ እንዲሆን ነው። በዛሬው ጥናታችን ኤፌ 1፡1-14 ያለውን በሰፊው ተመልክተን እግዚአብሔር በሁሉ ለምን መከበር እንዳለበት እናያለን።

## 1. የአማኞች ሁለት አድራሻ (ኤፌ 1፡1-2)

ሐዋሪያው ጳውሎስ በኤፌ 1፡1-2 ባለው በመጀመሪያ ለኤፌሶን ቅዱሳን ሰላምታውን ያቀርባል - በዚህም (ዛሬ እኛንም ጨምሮ) ሁለት አድራሻ እንዳላቸው ያመላክታል። "በኤፌሶን ያሉ ቅዱሳን" (ምድራዊ ቤ/ክ) ሲል፣ በአንድ በኩል አማኞች ምድራዊ መኖሪያ ያላቸው መሆኑን ሲያሳስብ፣ "በክርስቶስ ኢየሱስም ላሉ ምዕመናን" (ሰማያዊ) ሲል ደግሞ በሌላ በኩል አማኞች መንፈሳዊ አድረሻ እንዳላቸው ያሳስባል። ስለዚህም አማኝ በዚህ ምድር ሲኖር ሁልጊዜ ሁለተኛ አድራሻ እንዳለው አውቆ የሰማዩን እያሰበ ሊኖር ይገባዋል። ይህ ደግሞ ስለ አህዛብና አይሁድ በክርስቶስ ድነት ለማመልከት መንደርደሪያ ሃሳብ ነው (ከምዕራፍ 2 በኋላ እናያቸዋለን)።

## 2. እግዚአብሔር ሊከበር የሚገባበት ምክንያት (ኤፌ 1፡3-14)

**ኤፌ 1፡3** ሐዋሪያው ጳውሎስ "በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከቶች ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።" ሲል የዚህን አንቀጽ ዋና አሳብ ያስጨብጣል። እግዚአብሔር አማኞችን በመንፈሳዊ በረከቶች ስለባረከን እሱ ደግሞ እንዲሁ ሊባረክ ይገባል።

**ኤፌ 1፡4- 14** ባለው እግዚአብሔር ይከብር እና ይባረክ ዘንድ፣ በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ሥራ አማኞች እንዴት እንደተባረከን ይዘረዝራል።

### 2.1) እግዚአብሔር ይከብር ዘድ በእግዚአብሔር አብ የተሰጠን መንፈሳዊ በረከት ( **ኤፌ1፡4-6)**

በዚህ ክፍል ውስጥ ሐዋሪያው እግዚአብሔር አብ በእኛ ድነት ውስጥ የነበረውን ድርሻ ይዘረዝራል። በመጀመሪያ ዓለም ሳይፈጠር በፊት በክርስቶስ ከኃጢአታችን ነጽተን ቅዱሳን ሆነን እንድንኖር የመረጠን እግዚአብሔር ነው። የድነት እቅድ ባለቤት ራሱ እግዚአብሔር ነው። ያለ እግዚአብሔር ምርጫ እና ጥሪ ባይሆን ዛሬ ድነት በእኛ ጉልበት የማይታሰብ ነበር። በሁለተኛ ደረጃ፣ ይህ እኛን ለማዳን የነበረው የእግዚአብሔር አላማ በእኛ ጥረት ሳይሆን፣ በክርስቶስ ሥራ የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆን የወሰነው እግዚአብሔር ነው። ስለዚህም በአጭሩ እኛ ወደ ድነት እንድንደርስ የመረጠን እና የወሰነን እግዚአብሔር ነው።

በዚህ ሁሉ ግን የእግዚአብሔር አላማው ምንድን ነው? ብለን ብንጠይቅ፣ ጳውሎስ እግዚአብሔር ይህንን ያደረገው **"የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህንን አደረገ"** ሲል የእግዚአብሔር ዓላማ በስተ መጨረሻው "የጸጋው ክብር" ራሱ እንግዚአብሔር እንዲከበርበት እንደሆነ ያሳየናል።

## 2፡2) እግዚአብሔር ይከብር ዘንድ በእግዚአብሔር ወልድ የተደረገልን በረከት (ኤፌ1፡7-12)

ከቁ 7-11 ባለው እግዚአብሔር አብ ያቀደው እና የወሰነው ውሳኔ ወደ እውነት እንዲመጣ በክርስቶስ ኢየሱስ የተቀበልነውን መንፈሳዊ በረከቶች ይዘረዝራል። በመጀመሪያ በደሙ የተረገ ቤዛነታችንን አገኘን። ክርስቶስ እኛ ልንሞት የሚገባውን ሞት ሞቶ ዋጋችንን ከፈለ፣ እሱ ባፈሰሰው ደም እኛ ኃጢአታችን ይቅር ተባለ። በሁለተኛ ደረጃ፣ ከመዳናችን ሌላ የእግዚአብሔርን አላማ ማወቅ እና መረዳት እንድንችል ጸጋ ተሰጠን። ስለዚህም ዛሬ መዳናችንን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ለወደፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ያቀደልንን ሁሉን በክርስቶስ ኢየሱስ ሊጠቀልል እና ሊገዛ እንዳለ መረዳት ቻልን። በሦስተኛ ደረጃ ርስትን ተቀበልን። ክርስቶስ በስራው ሥራ የማያልፍ እና ለዘላለም የሚሆን ርስት ተሰጥቶናል።

ጳውሎስ በቁ 12 ላይ በድጋሚ በክርስቶስ ኢየሱስ የተደረገልንን ነገር በሙሉ ለምን እንደተቀበልን ሲናገር "በክርስቶስ አስቀድመን ተስፋ ያደረግን እኛ ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው" ይላል። የእግዚአብሔር ዋነኛው አላማ እኛ እንድንድን እና እንድንደሰት ብቻ ሳይሆን በነገር ሁሉ እግዚአብሔር እዲከብር ነው።

## 2፡3) እግዚአብሔር ይከብር ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ የተደረገልን በረከት (ኤፌ 1፡ 13-14)

በመጨረሻ ከቁ. 13-14 አማኞች በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው ሲድኑ በመንፈስ ቅዱስ የሚቀበሉትን መንፈሳዊ በረከት ይገልጻል። አማኝ ጌታ በሚቀበልበት ቅጽበት ከእንግዲህ ወዲህ የእግዚአብሔር መሆኑን ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ በማተም ያሳስባል። ቅዱሱ የእግዚአብሔር መንፈው በአማኙ ውስጥ ያድራል። ያ ቅዱስ መንፈስ እግዚአብሔር ለአማኝ የሰጠውን ተስፋ እንደሚፈጽም የሚያሳስብ መያዣ ሆኖ ዛሬ ያገለግላል።

እንደገና መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ውስጥ ሆኖ ዛሬ የሚሰራውን ስንመለከት መንፈስ ቅዱስም ይህንን የሚያደርገው "ለእግዚአብሔር ያለው ሁሉ እሲኪዋጅ ድረስ ክብሩ ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሆን ዘንድ" ነው (ኤፌ1፡ 14)።

እንግዲ እግዚአብሔር በድነታችን ውስጥ የሰራውን እና የሚሰራውን ስንመለከት እንዲሁ አማኝ ደስ ብሎት ብቻ እንዲኖር ሳይሆን በሁሉ እግዚአብሔር እንዲከብር ነው።

## *መደምደሚያ*

እግዚአብሔር ያዳነን ለግል ደስታችን ብቻ አይደለም። በርግጥ በእግዚአብሔር ማዳን ደስ እንሰኛለን ደግሞም በእግዚአብሔር ተስፋ እናደርጋለን። ሆኖም ግን እግዚአብሔር እኛን ያዳነበት ዓይነተኛው ምክንያት ግን በሁሉ ነገር እሱ እንዲከብር ነው። ስለዚህም ዛሬ በምንኖረው ኑሮ በተቀዳሚነት ልናስበው የሚገባን የራሳችን ደስታ፣ ትርፍ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ክብር መሆን እንዳለበት ልናስብ ይገባናል። እንደ ክርስቲያን ሁለት ዓይነት አድራሻ እንዳለን ማወቅ አለብን (ሰማያዊና እና ምድራዊ)።

## *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. ከመግቢያ ስለ ኤፌሶን ከተማና ስለ ኤፌሶን መልዕክት ምን ተረዳን?
2. ከኤፌ 1፡1-3 በመነሳት አማኞች ሁለት አድራሻ እንዳላቸው የሚያስረዳን ምን ፍንጭ አለ? አድራሻዎቹስ ምንድን ናቸው? ልዩነታቸውስ ምንድ ነው?
3. ኤፌ 1፡ 3 ላይ ጳውሎስ እግዚአብሔር "በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ" እንደባረከን ይናገራል።

እግዚአብሔር አማኞችን የባረከበት መንፈሳዊ በረከቶች ምንድን ናቸው? ኤፌ 1፡3- 14 ያለውን ያለውን በማንበብ መልሱ።

4. ኤፌ 1፡3-14 ባለው እግዚአብሔር አማኞችን በመንፈሳዊ በረከት ሲባርክ አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ በዚህ እንደተሳተፉ እናነባለን። በዚህ መንፈሳዊ በረከት ውስጥ የእያንዳንዱ የስላሴ አካል ድርሻ ምንድን ነው? የአብ ድርሻ (1፡4-6)፣ የወልድ ድርሻ (1፡7-12)፣ የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ (1፡13-14)

5. ኤፌ 1፡3፣ 6፣12 እና 14 መሰረት እግዚአብሔር እኛን ያዳነበት እና በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከት ምክንያት ምንድን ነው?

6. ኤፌ 1፡3፣ ቁ.6፣ቁ.12 እና ቁ.14 መሰረት እግዚአብሔር እኛን ያዳነበት እና በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከት ምክንያት ምንድን ነው?

7. ከዛሬ ጥናት ምን ተማርን? እግዚአብሔር ሁሉን ያደረገው ለራሱ ክብር ከሆነ ዛሬ በሚኖረን ሕይወት እና ኑሮ ከኛ የሚጠበቀው ምንድን ነው?

# ጥናት ሁለት

ኤፌ 1፡14-23

## የልባችን አይኖች ይበሩ ዘንድ

## ዓላማ፡-

የልባችን አይኖች በርተው የተጠራንበት ተስፋ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ማየት የመቻል ጥማት በውስጣችን እንዲያድር መርዳት።

## መግቢያ

ባለፈው ጥናታችን አማኝ ሁለት ዓይነት አድራሻ ማለትም ምድራዊና ሰማያዊ (መንፈሳዊ) እንዳለው ተመልክተን ነበር። ክርስቲያን ሁለት ዓይነት አድራሻ ብቻ ሳይሆን ሁለት አይኖችም ነው ያሉት። በምድራዊ አይኑ ምድራዊ የሆኑ ነገሮችን፣ ቁስ አካል እና ቀለም ያላቸውን ነገሮች ማየት ሲችል፣ በመንፈሳዊ አይን ግን ሰማያዊውን እና የእግዚአብሔር የሆነውን ነገር ማስተዋል ይችላል።

## የድነትን እጅግ ከፍ ያለውን ክብር ለማወቅ መነፈሳዊ ዓይን ሊበራ ይገባል

ባለፈው ጥናታችን ጳውሎስ በሁሉ ነገር መጨረሻ እግዚአብሔር ራሱ እንዲከብር፣ እግዚአብሔር አማኞችን ስለ ባረከበት በረከት የጻፈውን አጥንተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ጳውሎስ የኤፌሶን አማኞች መንፈሳዊ አይኖቻቸው እንዲበሩ የጸለየላቸውን ጸሎት እንመለከታለን። በዚህም ጥናታችን የመንፈሳዊ አይኖችን ወደር የሌለው ጥቅም አስተውሎ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች እንደጸለየላቸው እንዲሁ እኛም ጥማታችን እና ልመናችን አይኖቻችን በርተው መንፈሳዊውን እና ለዘለዓለም የሆነውን እንድናስተውል ይሁን።

## የኤፌሶን ሰዎች እንዲያውቁ የሐዋርያው ጳውሎስ ጸሎት። ስለ ምን እንዲያውቁ?(1፡15-19)።

ሐዋሪያው ጳውሎስ በጸሎቱ ጊዜ ስለ ኤፌሶን ሰዎች  እንደሚያመሰግን እና እንደሚለምንላቸው ይገልጻል (15-19)። በአንድ በኩል በዚያ ያሉት አማኞች በክርስቶስ ኢየሱስ ባላቸው እምነት የበረቱ ብቻ ሳይሆኑ፣ ለቅዱሳንም ታላቅ ፍቅር ያላቸው በመሆናቸው ጳውሎስ ስለ እነዚህ አማኞች እግዚአብሔርን እጅግ ያመሰግናል (ኤፌ 1፡15-16፣ሪዕይ2፡4)። በእርግጥም በሐዋ 20፡31 ላይ እንደምናነበው እነዚህን አማኞች ለማሳደግ ጳውሎስ ሦስት አመት **"ቀን እና ሌሊት"** እንደደከመ እናውቃለን። አሁን የድካሙ ውጤት መልካም ሆኖ አማኞቹ በእምነታቸው የበረቱ እንዲሁም እርስ በእርስ ለቅዱሳን ባላቸው ፍቅር የተመሰከረላቸው መሆኑ እግዚአብሔርን የሚያስመሰግን ነው።

ሆኖም ግን የክርስቲያን እድገት ማብቂያ የለውም! ስለዚህም ጳውሎስ አሁን ካሉበት ደረጃ እና እድገት የበለጠ እንዲያድጉ እና እንዲያውቁ  ይጸልይላቸዋል።

**ኤፌ1፡17-18** ላይ ያለውን የጳውሎስን ጸሎት አስተውለን ከተመለከትን ጳውሎስ እግዚአብሔርን የሚለምነው ሁለት ነገሮችን እንዲያደርግ ነው - 1. "የጥበብን እና የመገለጥን መንፈስ" እንዲሰጣቸው፣ እንዲሁም 2. "የልባቸው አይኖች እንዲበሩ" ።  እግዚአብሔር ይህን እንዲያደርግ ጳውሎስ የሚለምንበት ምክንያት (የጸሎት ርዕሶች) **1ኛ** እግዚአብሔርን ይበልጥ እንዲያውቁት **2ኛ** የተጠሩለት ተስፋ ምን እንደሆነ እንዲያውቁ **3ኛ** ለአማኞች ቃል የተገባውን የርስቱን ባለጠግነት እንዲያውቁ እና በስ ተመጨረሻም **4ኛ** እግዚአብሔር ለሚያምኑ ያለውን የኃይሉን ባለጠግነት እንዲያውቁ ነው። በአጭሩ ከዚህ ጸሎት የምንማረው ነገር፣እግዚአብሔር የልባችንን አይኖች ካላበራ እና የጥበብን መንፈስ ካልሰጠ በስተቀር፣ ሰው በራሱ የእግዚአብሔር የሆነውን መንፈሳዊ እውነት በራሱ ጉልበት ሊረዳ እና ራሱን እና ሕይወቱን ለዚህ እውነት ማስገዛት አይችልም። ስለዚህም ጳውሎስ በኤፌሶን ሰዎች

መካከል የተጀመረው መልካም እንቅስቃሴ በእግዚአብሔር መንፈስ እና አብርኾት ብርሃን እዲቀጥልና ይበልጥ እግዚአብሔርን በማወቅ እና የእግዚአብሔርን ነገር እንዲያስተውሉ ይጸልይላቸዋል።

## እግዚአብሔር ለሚያምኑት ያለው የኃይሉ ታላቅነት (1፡19-23)

ከላይ እንደተመለከትነው ጳውሎስ ስለ ኤፌሶን ሰዎች የልባቸው አይኖች እንዲበሩ የጸለየበት ምክንያት አንዱ እግዚአብሔር ለሚያምኑ ያለውን ኃይል እንዲያውቁ ነው (ቁ. 19-18)። ምናልባት እግዚአብሔር ለሚያምኑት ያለው **ኃይል ምን ያህል ታላቅ ነው? ምንስ ያደርጋል? ብለን ብንጠይቅ ጳውሎስ ከዚህ በኋላ ባለው መልስ ይሰጣል**። ይህ ኃይል ክርስቶስን ከሞት አስነስቶ ዛሬ በእግዚአብሔር ቀኝ ያስቀመጠው ኃይል ነው። ስለዚህም ዛሬ አማኝ በጌታ ሆኖ በአካል ቢሞት እንኳ እግዚአብሔር ከክርስቶስ የገለጠው ኃይል ለሚቹም እንዳለው ማወቅ ይችላል። ክርስቶስ ከሞት ያስነሳው ያው ጉልበት በጌታ ቀን ሚቹን አማኝ ከሞት ያስነሳል። ይህ እግዚአብሔር ለሚያምኑት ያለው ኃይል ክርስቶስ ከሞት ያስነሳው ብቻ ሳይሆን "ከግዛት እና ከሥልጣን፣ ከኀይል እና ከጌትነት እንዲሁም በአሁኑ ዘመን ብቻ ሳይሆን በሚመጣውም ዘመን ቢሆን ሊሰየም ከሚቻለው ስም ሁሉ በላይ" ያሰየመው ኃይል ነው። እግዚአብሔር ሁሉን ከክርስቶስ እግር ስር ሲያስገዛ አለማትን እና ስልጣናት ብቻ ሳይሆን የክርስቶስ አካል እና "ሙላት" የሆነችውን ቤተክርስቲያንንም ጭምር ነው። ልክ እንዲሁ እግዚአሔር ለሚያምኑቱ ያለው ኃይል አማኝን አንድ ቀን ከሞት የሚያስነሳ ብቻ ሳይሆን ከክርስቶስ ጋር አብረው እንዲነግሱ እና እዲገዙ የሚያደርግ ኃይል ነው።

## የአማኝ ዓይን ምን ማየት አለበት?

አማኝ አይኑ ያለው የዛሬው ጉዳይ ላይ እና ምድራዊው ላይ ብቻ ከሆነ ሕይወቱ በዚሁ ምድራዊ ነገር ላይ ያተኮረ ብቻ ይሆናል። ነገር ግን አማኝ ከዛሬው ምድራዊ ሕይወት በላይ ማሰብ እና መኖር መቻል ይገባዋል። ለዚህም ነው ጳውሎስ ስለ ኤፌሶን ሰዎች የልቦናቸው አይኖች እንዲበሩ እና የእግዚአብሔርን ነገር እንዲያስተውሉ መጸለዩ። እኛም ዛሬ በዚህ ሕይወታችን የልቦናችን ዓይኖች በርተው የሰማዩን ነገር እንዲያዩና እንዲያስተውሉ ጥማታችንና ጸሎታችን እንዲሆን ይገባል።

## መደምደምያ

በድጋሚ አማኝ ሁለት አድራሻ ያለው ነው። ምድራዊ አድራሻ ያለው እንደመሆኑ ለምድራዊ ነገር የሚገባውን ሁሉ ሊያደርግ እና ምድራዊ ሕይወቱን ሊመራ ይገባል። ነገር ግን ለአማኝ ሕይወት ምድራዊ ብቻ አይደለም። መንፈሳዊ አድራሻ ያለው እንደመሆኑ መንፈሳዊውን ነገር ሊያይ እና ሊያስተውል ይገባል። ለዚህም ነው ጳውሎስ በሌላ ቦታ አማኞችን "እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፥ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ" ቆላ 3፡1 መምከሩ። እንግዲህ እንደ አማኝ ልቦናችን መንፈሳዊውን ነገር እንዲያይ እና እንዲጠማ ጸሎታች ሆኖ እግዚአብሔር የልቦና አይኖቻችንን ያብራልን።

## ወደ መወያያ ጥያቄዎች ከመሄዳችን በፊት የሐዋ ጳውሎስን ጸሎት በደንብ ይነበብ (ኤፌ 1፡14-23)።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ምንም እንኳ ጳውሎስ ስለ ኤፌሶን ሰዎች የሰማው መልካም ዜና እግዚአብሔርን የሚያስመሰግን ቢሆንም ግን ይበልጥ እንዲያድጉ እግዚአብሔር የልቦና አይናቸውን እንዲያበራ ይጸልያል። ይህ ስለ መንፈሳዊ እድገት ምን የሚያስተምረን ነገር አለ?

2. ጳውሎስ ከጸለያቸው ጸሎቶች አንዱ የኤፌሶን አማኞች እግዚአብሔርን ይበልጥ ያውቁት ዘንድ እግዚአብሔር "የጥበብን እና የመገለጥን መንፈስ" እንዲሰጣቸው ነው። ይህ የጥበብ እና የመገለጥ መንፈስ ምንድን ነው? እግዚአብሔርንስ እንዲያውቁት የሚረዳቸው እንዴት ነው?

3. የልቦና አይን ምንድን ነው? ይህስ የልቦና አይን ሲበራ በአማኞች የሚያመጣው ለውጥ ምንድን ነው?

4. ጳውሎስ የመጥራቱን ተስፋ እና የርስቱን ባለጠግነት እንድታውቁ የልቦናቸሁ አይኖች እንዲበሩ እጸልያለው ይላል። በዚህ መሰረት እግዚአብሔር እኛን የጠራበት ተስፋ እና የርስቱ ባለጠግነት ምንድን ነው?

5. ጳውሎስ በጸሎቱ የአማኞቹ የልቦና አይኖች እንዲበሩ የጸለየበት ምክኒያት አንዱ እግዚአብሔር ለሚያምኑ ያለውን ኃይል እንዲያውቁ ነው። ይህ ኃይል ምንድን ነው? በአማኞች ሕይወትስ የሚሰራው ምንድን ነው?

6. በሥጋዊ አይኖች እና በልቦና (በመንፈሳዊ) አይኖች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

7. አማኝ የልቦናው አይን ሲበራ በሕይወቱ የሚኖረው ለውጥ ምንድን ነው? የልቦናው አይኖች አስተውለው እንዲያዩስ አማኝ ማድረግ ያለበት ምንድን ነው ትላላችሁ?መንፈሳዊ ዓይኖች ካልበሩ አደጋው ምንድ ነው?

8. የእኛስ ዓይኖች ምንድ ነው የሚያዩ? ከዛሬ ጥናት ምን ተማርን?

## ጥናት ሶስት

### የምንባብ ክፍል **ኤፌ 2፡1-10**

# ለሰው ሁሉ ከእግዚአብሔር የተገለጠው የድነት ጸጋ

## ዓላማ፡-

ለእያንዳንዱ ሰው ከእግዚአብሔር የተገለጠው የድነት ጸጋ፣ለግል የሆነ ጥሪ መሆኑና እንዲያውቅ

## መግቢያ፡-

ምዕራፍ አንድ ላይ የድነት እቅድ እንደተገለጠው ለተቀበለው ሰው ሁሉ በረከት ሆኖ በራሱ በእግዚአብሔር ለእራሱ ለእግዚአብሔር ክብር ነው። ይህም የተፈጸመው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ *ሥራ* ነው። ኤፌ ምዕራፍ 2 እና 3 የእግዚአብሔርን የጸጋውን ክብር የድነት ዓላማ ዳር ለማድረስ አይሁድም ሆነ አህዛብ ይህንን የጸጋውን ጥልቅ ምስጢር እንዲያውቁ ያሳስባል።

ከዚህ በፊት በነበረው ጥናት እንዳየነው ክርስቶስ የሁሉም ራስ በመሆን ቤ/ክንም የክርስቶስ አካል ሆና በድነት ጸጋ እንደተባረከች እና ለሰው ሁሉ ድነት ክብሩ ለእግዚአብሔር እንደሆነም ተወያይተናል።ከዚህ ቀጥሎ ያለው ክፍል ደግሞ በክርስቶስ በኩል ለሁሉ ሰው (ለአህዛብና ለአይሁድ) ስለተገለጠው **የድነት ጸጋ** እግዚ/ር *ሥራውን* እንደቀጠለና ይህንንም እንድናውቅ ያሳስባል። ስለ እግዚአብሔር ጸጋ አስባችሁ ታውቃላችሁ?

**ኤፌ 2፡1-10** ይህ ክፍል ከጌታ በፊት ጸጋውን ባላገኙ ጊዜ፤ ከጌታ ጋር ጸጋውን ባገኙ ጊዜና የወደ ፊቱን የክርስትና ህይወት ገጽታ የሚያሳይ ክፍል ነው።

## 1. በመንፈሱ የሞተ ሰው ባህርይ (መንፈሳዊ ሞት)

ቁ. 1 **"በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ..."**። ሰው እንደቆመ ይሞታል ማለት ነው? ሶስት ዓይነት ሞት እንዳለ ይታወቃል (*ሥጋዊ፣መንፈሳዊ፣ዘላለማዊ*) ከጌታ በፊት ጸጋውን ባላገኙ ጊዜ ይህ መልዕክት የተጻፈላቸው ክርስቲያኖች በመንፈስ ከእግዚ/ር የተለዩ ነበሩ። *መሞት ማለት መለየት ማለት ነው። ሥጋው ሞት* በሥጋ ሞት ከሰው መለየት ሲሁን መንፈሳዊ ሞት ደግሞ ከጌታ መለየት ነው።

የሰው ልጅ በኃጢአት ከወደቀ በኋላ በመንፈሱ ሙት ነው። ሮሜ 5፡12-15 "ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ...ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ፥ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ፤ አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው ለእርሱ አምሳሉ ነውና...በአንድ ሰው በደል ብዙዎቹ ሞተዋልና፥..." የሚለው ሃሳብ ኤፌ 2፡1ን ያጠናክራል። በብሉይ ኪዳን አይሁዳዊያን በእግዚአብሔር ሕግ ላይ አመጽ ከሰሩ የበደልና የኃጢአት መስዋዕት ያቀርቡ ዘንድ ታዘዋል። መስዋዕቱንም ያቀርቡ የነበሩት ባለ ማወቅና በማወቅ ለሚደረጉ ኃጢአትና በደል ከእግዚአብሔር ይቅርታ ለማግኘት ነበር (ዘሌ 4፡1-6፡7፣6፡24-7፡6)። እነዚህን መስዋዕቶች ሁሉም (ካህኑም ጭምር) እንዲይቀረቡ ተጠይቀዋል ዕብ 5፡1-6 "... 3 በዚህም ምክንያት ካህኑ ስለ ሕዝብ እንደሚያቀርብ እንዲሁ ስለ ራሱ ደግሞ መስዋዕትን ስለ ኃጢአት ሊያቀርብ ይገባዋል..."። ይህም ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ሕብረት ለጊዜው ያስተካክል ነበር።

## 2. በክፉ መናፍስት ዓለም ፈቃድ መመላለስ

**በክፉ መናፍስት ዓለም ፈቃድ መመላለስ ማለት ምን ማለት ነው?** ኤፌ 2፡2 "በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን **ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ**

***ፈቃድ፥ በፊት ተመላለሳችሁባቸው"።*** የሐ12፡31፣14፡30 በዚህ ክፍል ሰይጣን **"የዚህ ዓለም ገዥ"** ተብሏል። 2ቆሮ 4፡4 ደግሞ እንደሚከተለው ያስቀምጣል "ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፥ **የዚህ ዓለም አምላክ** የማያምኑትን አሳብ አሳወረ" ያልዳነውን በምንም የሥልጣን ደረጃ ያለውን ሰው ሰይጣን ልጠቀመው እንደሚችል እናውቃለን? ይህ መልዕክት እንደሚነግረን ጌታን ከማወቃቸው በፊት በሠይጣን ፈቃድ ለእግዚ/ር ባለመታዘዝ ይመላለሱ እንደነበሩ ነው። በሌላ አነጋገር የሰው ልጅ እግዚአብሔርን ሳይታዘዝ ሲቀር (ጌታ በህይወቱ ሳይኖረው ሲዋሽ፣ሲሰርቅ፣ሲታበይ ወዘተ) የኢጋንንት መጠቀሚያ መሳሪያ ሊሆን እንደሚችል ያስተምረናል። አይሁዳዊያን ደግሞ በትዕቢት እኛ እንሻላለን ብለው እንዲመኩ ያደርግ ነበር። ሰይጣን ሀሰተኛ ከሳሽና የክፉ መናፍስ ዓለም ሰራዊት መሪ ነው (ዮሐ 12፡31)። ሰዎችን ከእግዚአብሔር መንግስት ማራቅ ዋና ተግባሩ ነው። የኤፌሶን ሰዎች (አህዛብ) የከተማው የመናፍስት አምልኮ ልምምድም ነበራቸው።

## 3. የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ፡-

ኤፌ 2፡3 **"በእነዚህም ልጆች** መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ፥ ***የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ*** እያደረግን፥ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን። እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን" **"በእነዚህ ልጆች"** የሚለው ሀረግ የሚያመለክተን እግዚአብሔርን የማያውቁትንና በሥጋ የሞቱትን ሰዎች ነው።፡ ሥጋ ደግሞ ጽድቅንና እውነትን የማያስብ ማንነት ነው። ቁ.2 ላይ "***በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ"*** ሲል ቁ. 3 ላይ ደግሞ "***የሥጋችንንና የልቦናችንን ፈቃድ እያደረገን"*** ጌታን ከመቀበል በፊት የነበረውን ኑሮ ያብራራል። ሰው የሠይጣንንና የሥጋውን ምኞት ሲፈጽም ራሱን ለእግዚአብሔር ቁጣ ያዘጋጃል። ነገር ግን ማወቅ የሚገባን የሰው ልጅ በውስጡ ያለው የእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ መልካም ስነ ምግባር የማድረግ አቅም አለው። በርግጥ ይህ መልካም ሥራ ለድነት ሊያበቃው በፈጹም አይችልም። ስለዚህ ለዘላለማዊ ህይወት ሌላ ነገር ያስፈልገዋል። እርሱም በክርስቶስ የተዘጋጀው የድነት ጸጋ ነው።

## 4. ይህ ሁሉ የኃጢአት ችግር ካለ መፍተሄው ምንድ ነው?

**ኤፌ 2፡4-9 የ**እግዚአብሔር የምህረቱ ባለጠግነትነ ሁሉን ያሸንፋል። ቁ.4እና 5 ላይ የተጠቀሰው ዐ/ነገር እጅግ በጣም አስፈላጊ የሽግግር መልዕክት ነው። **ሽግግር ወዴት ቢባል**? የሞተውን ሰው ህያው የሚያደርግ መንገድ ሽግግር ነው። "ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለ ጠጋ ስለ ሆነ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ..." የሚል መልዕክት ቀጥሎ ያሉትን ቁጥሮች ያያይዛል። ከላይ ለተዘረዘሩ በኃጢአትና በበደል ምክንያት ከሚመጡ ችግሮችም ማምለጫ መንገዱን ይናገራል። ***<u>መንገዱም የራሱ ጸጋ በክርስቶስ በኩል የተሰጠ ነው</u>*** "በጸጋ ድናችኋልና"። "...ከእርሱ ጋር አስነሣን በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን" ቁ.7። ኢየሱስ ህይወት ነው። ኑሮአችንም በሰማይም ጭምር ነው።

በዚሁ ቁ7 ላይ **"በሚመጣው ዘመን"** የሚለው ሃሳብ ድነት ያለቀ ሆኖ ነገር ግን የሚፈጸምና በመጨረሻም ዋጋ ያለው መሆኑን ያሳያል (ኤፌ1፡21 ጋር ያገናዝቡ)። ነገር ግን ቁ.8 እንደሚነግረን ጸጋው ህይወት እንዲሰጥ **<u>እምነት</u>** አብሮት መኖር አለበት። እግዚአብሔር በምህረቱ የተገባንን ቂጣት አልሰጠንም። ነገር ግን በጸጋው በክርስቶስ ኢየሱስ ያልተገባንን ህይወት ሰጥቶናል። ሁሉ የሆነው ከእግዚአብሔር ነው። ማንም ሰው በራሱ ደግነትና ህግን በመጠበቅ ሕይወቱን ሊያድን አይችልም (ኤፌ 2፡9 "ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም" ሮሜ 3፡ 21፣28 አመሳክሩ")።

**ኤፌ 2፡10** "...***መልካሙን ሥራ ለማድረግ*** በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን" በመልካም ሥራዎቻችን አልዳንም ነገር ግን ለመልካም ሥራ ድነናል። የዳነ ሰው እምነት ሁል ጊዜ ለውጥ አለው። ኤፌ 2፡10 ከኤፌ 2፡2 ጋር አነጻጽሩ። ለዓለም፣ ለሰይጣን፣ለሥጋችንና ለልቦናችን ፈቃድ እየሰራን የነበርን አሁን መልካሙን ሥራ ለመሥራት ተለውጠናል። ***መልካም ሥራ ምንድ ነው?*** በጽድቅ ኑሮ ሌሎችን ማገልገልን ያጠቃልላል። ማገልገል ማለት በዘርና በወገን ሰውን ሳይለዩ ለሁሉም ከጨለማ ወደ ብርሃን ኑ ማለት ነው። በጌታ ሰዎችን በማዳን ሥራ ከመሳተፍ የሚበልጥ መልካም ሥራ የለም። እኛም ለዚሁ ነው የተጠራነው፤የተፈጠረው። "በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቼአለሁና" (ፊል 1፡6)።

## መደምደሚያ፡-

በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ህይወት ከመመረጡ በፊት ሰው ሁሉ ያለ ተስፋ ይኖር ነበር። አጋንንት ምንም እንኳን በጊዜና በቦታ የተወሰነ ቢሆንም ሰው ፈቃዱን ስሜቱንና እወቀቱን ለክፋ በሰጠ መጠን ይጠቀመው ነበር። ነገር ግን ብቻውን እግዚአብሔር በጸጋው የሰውን ልጅ ከዘላለማዊ ሞት አድኖታል፤እኛንም አድኖናል። በተጨማሪም የተጠራነውም መልካሙን የጌታን ሥራ (ሰውን በጌታ የማዳን ሥራ) እንድንሰራ ነው። በመልካም ሥራዎቻችን አልዳንም ነገር ግን ለመልካም ሥራ ድነናል። የዳነ ሰው እምነት ሁል ጊዜ ለውጥ አለው። ለዓለም፣ ለሰይጣን፣ለሥጋችንና ለልቦናችን ፈቃድ እየሰራን የነበርን አሁን መልካሙን ሥራ ለመሥራት ተለውጠናል (ኤፌ 2፡10 ከኤፌ 2፡2 ጋር እናነጻጽር)።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1 ኤፌ 2፡1 “በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ” ይላል። ሞት ማለት ምን ማለት ነው? ስንት ዓይነት ሞት መጥቀስ ትችላላችሁ?

2 ይህ መልዕክት በሕይወት ላሉ ሰዎች ነው የተጻፈው ብላችሁ ታስባላችሁ? ካላችሁ እንዴት ነበር ሙታን የነበሩ (እነደቆሙ ሞተዋል ማለት ነው) እንዴት?

3 ኤፌ 2፡2-3 መሰረት በማይታዘዙት ላይ የሚሰራው የመንፈስ አለቃ ምንድ ነው? ሥራውስ ምንድ ነው?

4 ኤፌ2፡2 ላይ “በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ” ሲል ቁ. 3 ላይ ደግም “የሥጋችንንና የልቦናችንን ፈቃድ” የሚለው ሃሳብ ምን አንድነትና ልዩነት አለው? እናብራራ።

5 ኤፌ 2፡4-9 መሰረት ለዚህ ሁሉ የኃጢአት ችግር መፍተሄው ምንድ ነው?

6 **ኤፌ 2፡7-10** በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርንበት ዓላማ ምንድ ነው? መልሳችንን እናብራራ።

7 ድነት በጸጋ ከሆነ የእኛ መልካም ሥራ ምን ያደርጋል (ኤፌ 2፡10 እና 2፡2ን እናነጻጽር)? መልካም ሥራ ምንድ ነው? ሰውን በሥጋዊ ነገር መርዳት ...ወይስ ምን?

8 ምን መልካም ሥራ እየሰራን እንደሆነ (ዛሬ የምስክርነት ጊዜ ይኑረን)?

# ጥናት አራት

አይሁድም ሆነ አህዛብ በክርስቶስ አንድ አካል ነው; **ኤፌ 2፡11-22**

## ዓላማ፡-

የእግዚአብሔር ጸጋ በክርስቶስ ኢየሱስ ለሁሉም ማለትም ለአህዛብም ሆነ ለአይሁድ እንዴት እንደተገለጠ ማሳወቅ፡፡

## መግቢያ፡-

አንድ ሰው እንደተናገረ ከ1500 እስከ 1850 ዓ/ም በነበሩት ዓመታት በዓለም ለይ 750 የሚያህሉ የሰላም ስምምነቶች ወይም ቃል ኪዳኖች ተደርገዋል፡፡ ነገር ግን አንዱም ከሁለት ዓመት በላይ ሳይዘልቅ ፈርሷል አለ፡፡ እግዚአብሄር ግን ከዘመናት በፊት **ለሰው ሁሉ የገባው የድነት ቃል ኪዳን** አልፈረሰም፡፡ በባለፈው ጥናት የእግዚአብሄር የድነት ቃል ኪዳን ለሁሉም እንዴት እንደተገለጠ አይተናል፡፡ አሁን ደግሞ አህዛብን በተለይ እንዴት በዚህ ቃል ኪዳን ወይም የእርቅ ጸጋ እግዚአብሔር እንዳቀላቀላቸው እናያለን፡፡ በኤፌሶን ቤ/ክ ብዙ በሥጋ ከአይሁድ ውጪ የሆኑ አማኞች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ አንዱ ለሌላው የነበራቸው እውቀትና አመለካከት የተሳሳተና እግዚአብሔር እንደሚያየው አልነበረም፡፡

## በክርስቶስ አንድ መሆን - ኤፌ 2፡11-17

**1. ስለ አህዛብ የአይሁዳዊያን እውቀት እና አመለካከት ኤፌ 2፡11 "…ይህን አስቡ"** ምን የሚል ጥያቄ ቢነሳ፣ በመገረዝ ቃል ኪዳን ውስጥ ያላለፉትን አህዛብን የተገረዙት አይሁዳዊያን ይንቁአቸው እንደነበረ ለማስታውስ የገባ ሐረግ ነው፡፡ **አይሁዳዊያን "ሴትና አህዛብ ስላላደረከኝ አመስግናለሁ" ብለው አምላካቸውን ያከብራሉ ይባላል፡፡** በተጨማሪም ወደ ቁ.12 ይሸጋገራል፡፡ ቁ.12 ላይ **አምስት** አሉታዊ ነገሮችን ስለ አህዛብ ይናገራል፡፡ 1. ከእስራኤል መንግሥት የራቁ 2. ለተስፋውም ቃል ኪዳን እንግዶች የሆኑ 3. በዚህም ዓለም ተስፋን ያጡ 4. ከእግዚአብሔርም የተለዩ 5. ያለ ክርስቶስም የነበሩ እንደሆኑ ይነግራቸዋል፡፡ እነዚህ ነገሮች ምን ያህል ከእግዚአብሔር መንግስት አርቋቸው እንደነበርና ግን የጌታ ጸጋ ከዚህ በላይ ታላቅ እንደሆነ እንዲገነዘቡ ለአህዛብ ያስተምራቸዋል፡፡ አይሁዳዊያንም ስለ አህዛብ በእግዚአብሔር የድነት እቅድ ላይ የተሳሳተ ግንዛቤ እንደነበራቸው ከዚህ ማወቅ ይቻላል (ድነት በመገረዝና ሕግን በመጠበቅ ይገኛል ብሎ በትዕቢት ማሰብ አንዱ ድክመታቸው ነው)፡፡

**2. የኤፌሶን አህዛብ የነበራቸው አምልኮ እና የአይሁዳዊያን ጥሪ፡-** አይሁዶች የተጠሩት በመለየታቸው ለሌሎች ህዝብ ጽድቅና ቅድስናን ማሳየት እንዲችሉ ነው፡፡ ነገር ግን ይህንን ማድረግ አልቻሉም፡፡ በተጨማሪም የኤፌሶን አህዛብ "ዳያና" የሚባል የጣኦት አምላክ ያመልኩ እንደነበረ ይታወቃል፡፡ ይህ ጣኦት በሴት ስም የምትጥራ ጣኦት ናት፡፡ ጥቅሟም ለመውለድና ለአደን ይሆናል ብለው ያምናሉ፡፡ "ዳያና" የሮማዊያን ጣኦት ስትሆን "አርጤምስ" ተመሳሳይ የግሪኮች ጣኦት ናት፡፡ ከዚህ ሁሉ አህዛብን የጌታ ጸጋ ነጻ አውጥቷቸዋል፡፡

3. **አንድ አዲስ ሰው**

"… **በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል"** ቀ.13 ላይ የራቁትን ወደ እግዚ/ር ያቀረባቸውን ዋናውን ምክንያት ይነግራቸዋል (የክርስቶስ ደም)፡፡ ቁ.12 ላይ **"በዚያ ዘመን"** ሲል ቁ.13 ላይ ግን **"አሁን ግን"** ብሎ በጌታ ሆነው ያገኙትን ጸጋ ያነጻጽራል፡፡ በነዚህ ሁለት ቁጥሮችና ቁ.17 ሶስት ጊዜ **"ርቃችሁ"** የሚል ቃል ተጠቅሟል፡፡ ከርቀት ጌታ በጸጋው እንዴት እንዳስጠጋቸውም ያሳያል፡፡ ሁለቱን ማዋሀድና የጥል ግድግዳ ማፍረስ የክርስቶስ ትልቅ ድል ነው፡፡እንደዚሁም ቁ.15 እና 16 ላይ "ጥል" የሚል ቃል ተደጋግሞ እናያለን፡፡ "**በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ…**" ቁ.15" የድሉ መሰረት ነው፡፡ ይህ ቃል እግዚአብሔር የሰጠውን የማይሻረውን

ህግ (ማቴ 5፡17 ሮሜ 3፡31) ሳይሆን ተጨማሪ አይሁዶች የጨምሩት የወግና የባህል ህግ የለያቸው ግድግዳ መሆኑን ማመልከቱ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። 365 አታድርጉ ህጎችና 248 አድርጉ ህጎች ነበሩአቸው። በቤተ መቅደስም በአህዛብና በአይሁዳዊያን አደባባይ መካከል ግድግዳም ነበር። ይህንን ያለፈም ይቀጣል። "ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ" በዚህ ክፍል "**አንድ አዲስ ሰው**" እና ቁ.16 ላይም የተጠቀሰው "**ሁለታቸውን በአንድ አካል**" የሚለው የክርስቶስን አካል ቤተክርስቲያንን ያመለክታል።

**4. ሰላም ለሁሉም ያስፈልጋል (ኤፌ 2፡17)**

**ቁ.17 "የምስራች ብሎ ሰበከ"፡- ምንን ነው የምስራች ብሎ የሰበከው?** ሐዋ ጳውሎስ በዚህ ክፍል ሁለት ተቃራኒ ነገሮችን ማለትም **"ጥልና" "ሰላምን"** ይደጋግማል። ዓላማውም ክርስቶስ በመስቀሉ ሞት ለሁሉቱም ሰላም እንደሆነ ለማመልከት ነው። "ሰላም"ለሁሉም ያስፈልጋቸዋል ማለትም ሩቅም ይሁን ቅርብ ለነበሩ በሙሉ ሰላም ያስፈልጋል። ቅርቦች አይሁዳዊያን ሲሆኑ ርቀው የነበሩ ደግሞ አይሁድ ናቸው። ጌታ ኢየሱስ በዮሐ 20 ላይ ሶስት ጊዜ **"ሰላም ለእናንተ ይሁን"** አላቸው። ዮሐ 16፡33 ላይም "በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ ይህን ተናግሬአችኋለሁ" ይላል።ይህንን ንግግር የተናገረው ለአይሁዶች ነው። በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር የተጣላውን አህዛብንም ሆነ አይሁድን አስታረቀ። ሐዋ ጳው በሮሜ 14፡19 እንዲህ ይላል "እንግዲያስ ሰላም የሚቆምበትን እርስ በርሳችንም የምንታነጽበትን እንከተል" ሰላም ለሁሉ ያስፈልጋል።

**5. የሁለቱ ውህደት ወጤት-አንድ ቤተሰብ-የእግዚአብሔር መኖሪያ (ኤፌ 2፡18-21)**

ሁለቱም ሕዝብ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች በመሆን እንግዳና መጻተኛ መሆን አበቃ **"እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም" (ኤፌ 2፡19)**። ስለ አንድ ቤተሰብ ሲታሰብ በወስጡ ያለው ፍቅርና ሰላም ምሳሌያዊ ንግግር ነው። ቁ.20 "በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል..." ይህ አንደ አንድ ቤተሰብ ሥዕላዊ መግለጫ በመሆን ሐዋርያትና ነቢያት የሰበኩት የክርስቶስ ሞትና ትንሳዔን ያመለክታል። ኤፌ2፡21 ላይ **"በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ" የሚለው ቃል** የሚያመለክተው በመንፈሳዊ ሰውነት አብሮ በክርስቶስ ማደግን ነው (አይሁድም ሆነ አህዛብ)። (ኤፌ 4፡16 "ከእርሱም የተነሣ አካል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ፥ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ፥ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል" ያነጻጽሩ)። **"የእግዚአብሔር መኖሪያ"** እንደ ቤተ መቅደስም ዘይቤያዊ ንግግር የክርስቶስ አካል ማለት ነው። ሰው ሁሉ በክርስቶስ ከዳነ የጌታ መንፈስ ማደሪያ ይሆናል። ቁ.22 **"በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ"፡-** ቤ/ክ አብሮ ማደግን አብሮ ማገልገልን የሚጠይቅ የጌታ ቤት ነው። ይህ ደግሞ አይሁድንም አህዛብንም አይለይም። የኤፌሶን አህዛብ በዳያና የጣኦት ቤተ መቅደስ እና አይሁዶችም በእስራዔላዊያን ቤተ መቅደስ ወይም ምኩራብ ትምክህት ከኃጢአታቸው ተመልሰው በአንድ በክርስቶስ አካል መገጣጠምን ያሳያል።

## መደምደሚያ፡-

ክርስቶስ ኢየሱስ ዘላለማዊ የእግዚአብሔርን የድነት እቅድ ለአህዛብም ሆነ ለአይሁድ ገልጧል። ቤተክርስቲያን አብሮ ማደግንና ማገልገልን የሚጠይቅ የጌታ ቤት ነው። ለዚህ ተግባራዊነት አንዱ አንዱን እርስ በርስ በፍቅር ያገለግላል። የጥል ግድግዳን አስወግደን ሰላምን ለሁሉም መስበክ አለብን። በዘርና በነገድ መለያየት ሥጋዊ ሥራና ከጌታ ጋር የሚያጣላ ነው።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ኤፌ2፡11 ላይ "...በሥጋ በእጅ የተገረዙ..." የሚለው ለማን ነው? እነዚህስ ምንድ ነው ትምክህታቸው?
2. በክርስቶስ ያልነበሩ አህዛብ አጥተው የነበሩትን ነገሮች በዝርዝር ተወያዩ ኤፌ 2፡12።
3. ኤፌ 2፡13-14"ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ" ብሎ የሚለው ማንን ነው? እንዴት ነው የፈጠረው?
4. ኤፌ2፡20 "በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል..." ይህ መሰረት ምንድ ነው? ማን ነው የታነጸው?
5. ኤፌ 2፡21 "በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ" የሚለውን ትክክለኛ ትርጉም አብራሩ ኤፌ 4፡16 ጋር ያገናዝቡ።
6. ከዛሬው ጥናት ምን ተማርን? ጌታን የምናመስግን ነገር አለ?

# ጥናት አምስት

የምንባብ ክፍል፡ ኤፌ 3፡1-13

## የሐዋርያው ጳውሎስ የአህዛብ ሐዋርያነት የወንጌል ጥሪ ምስጢር

### ዓላማ፡-

እግዚአብሔር ለአህዛብ ከዘመናት በፊት የነበረውንና በልጁ የተፈጸመውን የድነት እቅድ በሐዋ ጳውሎስ ህይወት እንዴት እንደተፈጸመ የወንጌልን ታላቅ ምስጢር በትኩረት ማየት

### መግቢያ፡-

የሰው ዘር ለእግዚአብሔር ባለ መታዘዝ በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ከዘፍጥረት ምዕራፍ ሶስት ጀምሮ እግዚአብሔር እንደገና ከዚህ ባለመታዘዝ ምክንያት ከመጣው ሞት የማዳን የቃል ኪዳን እቅድ ነበረው። ይህም በብሉይ ኪዳን በተለያዩ ቦታዎች ተገልጧል፤ወደ ፍጻሜ ለማምጣትም የተለያዩ ሰዎችንም እግዚአብሔር ተጠቅሟል። በርግጥ በአዲስ ኪዳን ጌታ ይህን ታላቅ ምስጢር ለአህዛብ ለማስተላለፍ ብዙ ሰዎችን የተጠቀመ ቢሆንም ሐዋርያው ጳውሎስን ከሁሉም በላይ ማለት ይቻላል። "ጌታም፦ ይህ በአሕዛብም በነገሥታትም በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነውና ሂድ፤ስለ ስሜ ስንት መከራ ሊቀበል እንዲያስፈልገው እኔ አመለክተዋለሁና አለው" (ሐዋ 9፡15)። እግዚአብሔር አህዛብን ከአይሁድ ጋር አንድ የማድረግ የእግዚአብሔር መንግስት ምስጢር ታላቅ ነው። **ምስጢር የሚል ቃል በኤፌሶን መልዕክት 6 ጊዜ ተጠቅሷል፤ከነዚህ 3ቱ ያለው በምዕራፍ ሶስት ነው።**

ኤፌ 3፡1-6 ሁሉንም አንድ የማድረግ የእግዚአብሔር የድነት መለኮታዊ ምስጢር

1. **አንድ ቤት ሆኖ አብሮ መሰራት፡- ኤፌ 3፡1-3 "ስለዚህም..."** ይህ አገናኝ ቃል ከኤፌ2 መጨረሻ ቁ.22 ጋር ይገናኛል። ሃሳቡም እንዲህ ይላል "ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ **አብራችሁ ትሰራላችሁ"።** የሐዋርያው ጵውሎስ ጸሎቱም አህዛብ ከአይሁድ ጋር አብረው አንድ ቤት ሆነው እንዲሰሩ እና እንዲያድጉ ነው። ይህም ታላቅ ምስጢር ነው።

**2. የአንድነት ወንጌል (የእግዚአብሔር መንግስት ምስጢር) ስለ ሰበከ ታሰረ፡- 3፡1 "የክርስቶስ ኢየሱስ እስር የሆንሁ..."** ይህን መልእክት በጻፈበት ወቅት ሐዋርያው ጳውሎስ በሮም ከተማ እስር ላይ እንደነበረም ይታወቃል። የታሰረበትም ምክንያት ከኃጢአት ሞት ነጻ የሚያወጣውን ወንጌል ሰለሰበከ እንደሆነ ግልጽ ነው። የሐዋ ሥራ 9፡ 15-16 ጌታም ስለ ሐዋ ጳውሎስ ለሐናንያ እንዲህ አለው "ይህ በአሕዛብም በነገሥታትም በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነውና ሂድ፤ስለ **ስሜ ስንት መከራ ሊቀበል እንዲያስፈልገው እኔ አመለክተዋለሁና አለው**"።ይህንን ቁጥር አንብበን ሐዋ 21፡29ን እናብብ፡ "በፊት የኤፌሶኑን ጥሮፊሞስን ከእርሱ ጋር በከተማ አይተውት ነበርና ጳውሎስም ወደ መቅደስ ያገባው መስሎአቸው ነው"። ለሐዋርያው ጳውሎስ በኢይሩሳሌም ስደት ምክንያት የነበረው ከኤፌሶን አህዛብ ወደ አይሁድ ቤተ መቅደስ አስገብተሃል ተብሎ እንደነበር በዚህ ክፍል መሰረት ግልጽ ነው። የዚህም ስደት መጨረሻው ሮም መታሰር ነበር። ቢታሰርም ግን አህዛብም ሆነ አይሁድ በአንድነት እንደ አንድ ቤት መሰራት እንዲችሉ ጸሎቱ ነው (እንበረከካለሁ ይላል)።

**ኤፌ 3፡3 "አስቀድሜ በአጭሩ እንደ ጻፍሁ"** ይህ ሃሳብ ብዙዎች የኤፌ 1፡9-10 መልዕክት ማመልከቱ ነው ብለው ይስማማሉ ። **"ይህን ምሥጢር በመግለጥ አስታወቀኝ"**፦በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ምስጢር በመለኮታዊ መገለጥ ስለ ሰው ልጆች የበራው እውነት ነው።

የሮሜ መልዕክት በ16ኛው ምዕራፍ ላይ ይህንን ሃሳብ ያብራራል "እንግዲህ እንደ ወንጌሌ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስም እንደ ተሰበከ፥ ከዘላለም ዘመንም **<u>የተሰወረው</u>** አሁን ግን የታየው በነቢያትም መጻሕፍት የዘላለም እግዚአብሔር

እንደ አዘዘ ለእምነት መታዘዝ ይሆን ዘንድ ለአሕዛብ ሁሉ **የታወቀው ምሥጢር እንደ ተገለጠ መጠን ሊያበረታችሁ ለሚችለው ብቻውን ጥበብ ላለው** ለእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን" (ሮሜ16፡25-27)።

**3.ከእግዚአብሔር የተገለጡ ምስጢሮች፡-** በኤፌ3፡4-6 በተለይም ቁ.5 ላይ ሶስት ከእግዚ/ር ስለተገለጡ ምስጢሮች ይናገራል፣እነርሱም 1. አሕዛብ (ከአይሁድ ጋር) አብረው እንዲወርሱ የመደረጉ ምስጢር፥ 2. አህዛብና አይሁድ በአንድ አካል (ቤ/ክ) አብረው እንዲሆኑ የመደረጋቸው ምስጢር፥ 3. በወንጌልም መስበክ (አገልግሎት) በክርስቶስ ኢየሱስ በሆነ የተስፋ ቃል አብረው እንዲካፈሉ እግዚ/ር ያደረገውን የጸጋ ምስጢር ናቸው።

**4. የመገለጡ ምስጢር በሐዋርያው ህይወት፡- ኤፌ3፡7-9** ባለው ክፍልም ይህንኑ በአጽንኦት ያብራራል። ሐዋ ጳውሎስም ይህንን ምስጢር ለመግለጥ ለአህዛብ እንደተላከ ራሱን ግልጽ ያደርጋል። እግዚአብሔር በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ የሚገኝ ህይወት ብቻ ሳይሆን አይሁድንና አህዛብን በመካከላቸው የነበረውን ጥላቻ አስወግዶ አንድ የማድረግ ምስጢር ለሐዋርያው ጥልቅ ምስጢር ነው። ወንጌል የሥጋ ጥላቻና ጠላትነትንም ያስወግዳል። እርሱንም ይህንን ምስጢር እንዲገልጥ እግዚ/ር ጠርቶታል። ይህንኑ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች ያብራራል። የዚህ ምስጢር እውነት በቀደሙት ነቢያት የተገለጠ ነገር አልነበረም። በተጨማሪም በሥጋም በመካከላቸው ያለውን ንቀትና ትምክህት እግዚአብሔር የማስወገድ ዓላማ አለው።

**5. የቤ/ክ ክብር የተፈጸመ የእግዚአብሔር የዘላለም ሃሳብ ነው፡- (ኤፌ 3፡10-13)** ይህ ክብር በወንጌል አንድ የመሆን ምስጢር ውጤት ነው። የሁለቱም የአህዛብና የአይሁዳዊያን አንድነት በሰማያዊ ሥፍራ ለቅዱሳንም ሆነ ለክፉ ዓለም መላእክት መታየቱ (ቆላ 1፡16) እግዚአብሔር ውህደቱን እንዴት እንደገለጠ ያስደንቃል "...**በሰማያዊ ሥፍራ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት ትታወቅ ዘንድ"**። ጌታ ያን ጥበብ በቤ/ክ በኩል ሲያሳይ የእግዚአብሔርን አስደናቂ ጥበብ ያያሉ (1ጴጥ 1፡10-12)። ወይንም የክርስቶስን ሥልጣን የመዳን አዋጅ ለክፉዎች የጨለማው ዓለም በአየር ላይ የማሳየቱ ምስጢር የዳኑ ሰዎች ክብር የድል አዋጅ ነው (ቁ.10-11)። የጨለማው ዓለም በአየር ላይ እንዳለ የታወቀ ቢሆንም (ኤፌ 6፡12፣ዳን 9፡2-23 2ቆሮ 6፡4-6) ቤ/ክ ከዚያ በላይ ድል እንዳላት ያስገነዝባል። ይህም የእግዚአብሔር እቅድ የሁለቱም ውህደት በሆነችው ቤ/ክ በኩል እየተሰራ እንዳለ ይገልጣል። ሁለቱንም አንድ በማድረግ በወንጌል አዋጅ ውስጥ ሐዋርያው እየደረሰበት ያለው መከራ ክብር እንደሆነ እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል (3፡13)።

## መደምደሚያ

ድነት ታላቅ ምስጢር ነው። ይህ ታላቅ መለኮታዊ ምስጢር ደግሞ አህዛብንም አይሁድንም አንድ ያደረገና በመካከል ያለውንም የጥል ግድግዳ ያስወገደ አስታራቂ ኃይል ነው። ሐዋርያው ጳውሎስም ይህንን እጅግ ክቡር ምስጢር ለአህዛብ እንዲሰብክ በዚህም ምክንያት ህይወት እንዲያገኙ በአህዛብና በአይሁድም መካከል የነበረውን የጥል ግድግዳ በወንጌል ኃይል እንዲያፈርስ ተጠራ። ይህም ድል ለመንፈሳዊ ዓለም ሁሉ ታይቷል። ዛሬም ቤ/ክ (እኛ) ይህንን ምስጢር ወደ ዓለም ሁሉ ይዛ እንድትሄድ ተጠርታለች። መከራችንም ክብራችን ነው።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1 ኤፌ3፡1 “ስለዚህም…” የሚለው ቃል ምንን እንደሚያመለክት ተወያዩ (ኤፌ 2፡22 ጋር ይገናኛል ብላችሁ ታስባላችሁ)

2 በዚህ መልእክት “ምስጢር” የሚል ቃል ስድስት ጊዜ ተጠቅሷል። ሶስቱ በዚህ ምዕራፍ 3 ይገኛል። “የክርስቶስን ምሥጢር እንዴት እንደማስተውል ልትመለከቱ ትችላላችሁ” (ኤፌ3፡4) ብሎ እየተናገረ ያለው ምስጢር ምንድ ነው?

3 በኤፌ 3፡5 በምስጢሩ መገለጥ የተገኙትን ውጤቶችን ተነጋገሩ (ስንት ናቸው?)

4 ኤፌ 3፡10 ላይ “…በሰማያዊ ሥፍራ ውስጥ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት ትታወቅ ዘንድ፤” ብሎ ሲል እነዚህ አለቆችና ሥልጣናት እነማን ናቸው? የምትታወቀውስ ምንድ ናት?

5 ኤፌ 3፡10 “ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ አሁን በቤተ ክርስቲያን በኩል በሰማያዊ ስፍራ ውስጥ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት ትታወቅ ዘንድ” የሚለውን ሃሳብ አብራሩ

6 ኤፌ 3፡11-13 አንብባችሁ ዋናውን ነገር ተውያዩ

7 ቤ/ክ አይሁድንንና አህዛብን አንድ በማድረግ በእግዚ/ር እቅድ ምን ክፍል አላት?

8 ከዛሬው ጥናት ሁላችንም ምን ተማርን? ምን ዓይነት ክብርና ምን የማድረግ ኃላፊነት የተሰጠን ይመስላችሁሃል?

# ጥናት ስድስት

የምንባብ ክፍል፡ **ኤፌ 3፡14-21**

## መሰረታዊ በሆነ በክርስቶስ ፍቅር መኖር የጌታን የወንጌል ጥልቅ ምስጢር ለማወቅ ጉልበት ነው

## ዓላማ፡-

ጥልቅ ፍቅር ለአማኞች ህይወት አንድነት መሰረት ስለሆነ ለዚህ ፍቅር መጸለይ እንዳለበትና ይህም የእግዚአብሔርን የወንጌልን ምስጢር ለማውቅ ዋና ነገር እንደሆነ ማሳሰብ።

## መግቢያ፡-

እግዚአብሔር በአህዛብም ሆነ በአይሁዳዊያን አማኞች ሕይወት እየሰራ ያለውን ነገር በሚመለከት ሐዋ ጳውሎስ ከልቡ እንደሚጸልይ ይገልጻል። ለዚህም ለህብረታቸው መሰረት ፍቅር መሆኑን በጥብቅ ያሳስባል። መለኮታዊ ፍቅር በመካከላቸው ካለ እኔ አህዛብ ነኝ እኔ አይሁዳዊ ነኝ መባባል ያቆማል። ለዚህም ብርሃን ትልቅ የጸሎት ተጋድሎ ይጠይቃል።

**1. የእግዚአብሔር መንግስት ምስጢር በሙላት ለማወቅ ጸሎት ያስፈልጋል (የአዕምሮ ብርሃን)፡-** ኤፌ3፡14-15 የሚጀምረው **"ስለዚህ ምክንያት…"** ብሎ ነው። ይህ ሀሳብ ከኤፌ 3፡1 ጋር ይገናኛል "ስለዚህም አሕዛብ ስለ ሆናችሁ ስለ እናንተ የክርስቶስ ኢየሱስ እስር የሆንሁ እኔ ጳውሎስ ለእግዚአብሔር እንበረከካለሁ"። ይህ ምክንያት ከላይ ኤፌ 3፡1-13 የተጠቀሱትን ከመከራ በላይ ይህ ምስጢር ግልጽ እንዲሆን በቤተሰብ ፍቅር በአባት ፊት መንበርከክ አስፈላጊ እንደሆነ ማሳየት ነው። በኤፌ2 የተገለጠውን በክርስቶስ የተገኘውን አዲሱን የክርስቲና ማንነት መጠበቅ ያለበት ነገር ነው። **"እንበረከካለህ"** በአባት ፊት (ለሞቱትና ላሉትም ለጌታ ሰዎች በሙሉ አባት ነው) መንበርከክ የመገዛትን፣ የማክበርንና፣ የትህትናን ምሳሌ ያሳያል (ዳን 6፡10፣መዝ 95፡1-6፣ሐዋ 20፡36)። በልብም ይሁን በሥጋ መንበርከክን ያጠቃልላል። **ሁሉን ላዋኸደ ይህ ክብር ይገበዋል**። ግን ደግሞ ጌታን ማክበር ብቻ ሳይሆን ቀጣይነት ያለው አንድነትና ጥልቅ ፍቅር ያስፈልጋቸዋል። ስለዚህም ጸሎት ያስፈልጋቸዋል። አንድነትና ፍቅር ካልተያዘ ሊጠፉ የሚችል ነገር ነው።

**2. ጸሎቶቹ ምን ይመስላሉ ((ኤፌ 3፡16-19)፡-**

ዓላማውም በተለያዩ የህይወት ዘርፎች አንድ ለመሆን መጠንከርን ያጠቃልላል። **ጸሎቱን በቡራኬ ይጀምራል** "በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነከሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን ይስጣችሁ፤" **በውስጥ ሰውነት መጠንከር** ማለት ምን ማለት ነው? ሁለት ዓይነት ሰውነት አለን ማለትም የውጪ ሥጋዊ አካላችንና የውስጥ መንፈሳዊ አካላችን ነው። የውጪ አካል ጥንካሬ እንደሚያስፈልገው ሁሉ የውስጥ ሰውነታችንም መጠንከር አለበት። በዚያን ጊዜ የሥጋን ማንነት ፈተናን መቋቋም ይችላል። የጌታ መንፈስና እምነት በኃይል እንዲገለጥ እውቀታችንን፣ስሜታችንንና ፈቃዳችንን በየቀኑ ለጌታ ማስገዛት አንድ ለመሆን መሰራታዊ ነገር ነው። **የክርስቶስ ህልውና በልባቸው በሙላት እንዲመሰረት**(ኤፌ 3፡16-17 ሮሜ 8፡9-10)፡- ይህ ሌላው የጸሎት ርዕስ ነው። አንዱ ክብደት ያለው ነገር ቦታ ሲይዝ ወይም ሲሞላ ሌላው ቦታ ይለቃል። የጌታ መንፈስ በሙላት ሲኖር የሥጋ ሃሳብ እየከሰመ ይሄዳል።

**የጸና ቤት አይናወጥም**:- መሰረታችን በክርስቶስ ፍቅር ካልጸና ዘር መለያየት ቀላል ነገር ይሆናል።ለዚህም በፍቅር የጸና ህይወት ያስፈልጋል።ለጌታና ለሌሎችም ልባዊ ፍቅር ካለቸው ሰውን (አህዛብና አይሁድ) ከሰው አይለያዩም።

"**ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፥** ከመታወቅም

የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ" ክርስቶስ በሞቱ የከፈለው ፍቅር ምሳሌያቸው እንዲሆን ይጸልያል። **ክርስቶስ ለቤ/ክ ያለውን ፍቅር በእውቀት እንዲይዙ እናም በየቀኑ እንዲለማመዱ ያስፈልጋል** (ኤፌ 3፡18-19)። ጌታ ህይወቱን ሰጥቷል። ፍቅር ዋጋ የሚከፈል፣በእውቀት የሚያዝ፣ እና በጥበብ በሥራ ላይ የሚተገበር ነገር ነው። "እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ" ወደ እግዚ/ር ሙላት መድረስ እንዲችሉ (ኤፌ 3፡19) ፍቅር መሰረታዊ ነገር ነው። የጌታ ህልውና ሙላት ሰው ሲኖረው ለሥጋዊ ነገር አይረታም። በዚህ ልመና ጌታ ምን ያህል ዋጋ መክፈሉን ሰው ካየ አህዛብን ከአይሁድ አይለይም፤ደግሞም አይናናቅም። የጌታ ህልውና እንደየሰው ልምምድ ይለያያል። ብቻ ጌታ ከሰው ጋር ከሆነ ለሥጋዊ ነገር አይሸነፍም።

ኤፌ 3፡20-21 ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ጸሎቱ መሰማት ምን ያህል መታመን በእግዚ/ር እንዳለ እምነቱን ያሳውቃል፡-"እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራው ኃይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው ለእርሱ በቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ እስከ ትውልዶች ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን"። ሐዋርያው አሁንም ቤ/ክንን ያመጣል። ማለትም ቤ/ክ ለእግዚ/ር ምስጋና የምታቀርብ አካል ናት። የጌታን ድል የምታውጅ ናት።

## *መደምደሚያ*

አንዱ አንዱን ለመቀበል የክርስቶስ ሥርና መሰረት ያለው (ኃይል ያለው፣የጠለቀና ሙሉ የሆነ) ፍቅር ወሳኝ ነገር ነው። እንደዚህ ዓይነት ፍቅር ሲኖር ሰው እርስ በእርስ መቀባበል አይከብደውም። ማንኛውም ጊዜ መንፈሳዊነትን ለመጠበቅ ጸሎት ወሳኝ ነገር ነው። ጸሎት ደግሞ እንግዚአብሔር በልጁ በኩል እንደሚሰማ በማመን በእምነት የሚደረግ ነገር ነው።

## *የመወያያ ጥያቄዎች*

1) ኤፌ 3፡14 "ስለዚህ ምክንያት" ያለው ምንን ማገናኘት ፈልጎ እንደሆነ እናብራራ? "አባትና" "መንበርከክ" የሚሉትን ቃላቶች ለምን እንደተጠቀመ እንወያይ።
2) የዚህ ክፍል ጸሎት ማለትም **የኤፌ3:14-19** እና የኤፌ1፡16-19 ያለው ጸሎት ልዩነቱ ምንድ ነው?
3) የኤፌ3:14-19 በዚህ ክፍል ስለ ጸለያቸው የጸሎት ዓይነቶች ተወያዩ። ስንት የጸሎት ርዕሶችን አገኛችሁ? ምን ምንድ ናቸው?
4) የጸሎቱ ቁልፍ ዓላማ ምን ይመስላችሁሃል?
5) ሐዋ ጳውሎስ በጸሎቱ ላይ ያለውን እምነት ቁ.20-21ን በማንበብ ተወያዩ። ቤ/ክ ሥራዋ ምንድ ነው?
6) ዛሬ የተማርነውን እናካፍል።እኛስ የምንጸልየው ለምንድ ነው? በወር አንድ ጊዜ ጾም ጸሎት ትጸልያላችሁ? ካልሆነ ጀምሩ (መንፈሳዊ ብርሃን ለሁሉም መሰረት ነው)።
7) በቤተ ክርስቲያናችን መቼ መቼ ጸሎት እንዳላ ታውቃላችሁ? ለማያውቁ ንገሩአቸው። ኑ ወደ ጸሎት ፕሮግራሞች። ጌታ ይባርካችሁ።

# ጥናት ሰባት

በአንድነት ማገልገል: **ኤፌ 4፡1-16**

## የጥናቱ ዓላማ፡

ሁላችንም በተሰጠን ፀጋ እያገለገልን የሌሎችንም ፀጋ በመቀበል በአንድነት የኢየሱስ ክርስቶስን ቤተክርስትያን እሱ ወደሞተበት ፍፁምነት እንድናመጣት ለማበረታታት።

***መግቢያ፡-*** በዛሬው ጥናት ቤተክርስቲያን እያንዳንዱ ከተቀበለው ልዩ ልዩ ፀጋ የተነሳ ልዩነት ቢኖሩባትም አንድ የሚያረጉአትም ነገሮች እንዳሉ እናያለን። ሁላችንም የተሰጠንን ፀጋ በመጠቀም የተጠራንበትን ጥሪ በተግባር ስናውል ከሌሎች ቅዱሳን ጋር በአንድነት በመስራት መሆን እንዳለበት ይህ ክፍል ያሳያል። ከሁሉ በላይ አንድ የሚያደርገን ሁላችንም የምናመልከውና የምናገለግለው **አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን** ስለሆነ ነው። በተጨማሪም የአገልግሎታችን ግቡ አንድ ስለሆነ በመሃላችን አንድነት መኖር እንዳለበት እናያለን። በሚቀጥሉት ምዕራፎች በጸጋ የተቀበልነውን ድነት መኖር እንዳለብን ያሳስበናል።

ኤፌ 4፡1 **"ለተጠራችሁበት መጠራት እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ"** ማለት ሰው የተጠራበት ጥሪ ሁል ጊዜ ከሰውየው የሚጠብቀው ተገቢ ስርዓት ወይም ኑሮ መኖሩን ያሳያል። ለምሳሌ አንድ ሰው አንድ መስሪያ ቤት ተቀጥሮ ሲገባ ስራውን ከመስራቱ በተጨማሪ ከስራ ባልደረቦቹ ጋር ሊኖረው የሚገባ ስርዓት አለ። እንደ መስሪያ ቤቱና እንደ ስራው አይነት ደግሞ ስርዓቱ ይለያያል። በዚህ ጥናት እንደምናየው የተጠራነው ጌታ እራሱ በሰጠን ፀጋ ከሌሎች ቅዱሳን ጋር ቤተክርስቲያንን ወደ ፍፁምነት ማምጣት ነው። ይህ ደግሞ ከኛ የሚጠብቅ ነገር አለ። እንደፈለግነው መኖር አንችልም።

**ኤፌ 4፡2~3** ለጥሪያችን ተገቢ የሆኑት ባህሪያት በነዚህ በሁለት ቁጥሮች ውስጥ ተገልጠዋል።

**ትሕትና፡** የምናገለግልበት ፀጋ የተሰጠን እንጂ የእኛ እንዳልሆነ አውቀን ራሳችንን ከማንም ሳናስበልጥ እኔ በራሴ ምንም ማድረግ አልችልም ብሎ ማለት ነው። ጌታ ትሁት ነበር (ፊል2፡1-8)።

**የዋህነት**፡ የሌሎችን ስራ በመልካም ማየት መቻል ነው። ቅዱሳን የሚያደርጉት ነገር ከበጎ ልብ እንደወጣ አስበን እነሱን በፍቅር ማየት። አመለካከታችን ንጽህ መሆን አለበት።

***ትዕግሥት***፡ ቅዱሳን ሲያጠፉ ስናይ ከመፍረድና ለጌታ የቀናን መስሎን እነሱን ከመጉዳት በፍቅር ጥፋታቸውን ይቅር እያልን ስህተታቸውን እንዲያዩና እንዲያስተካክሉ መርዳት።

***"እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሡ"*** የሚለው ሁላችንም ልናጠፋና ልናበላሽ ስለምንችል እኔም ልታገሥ ሌሎችም እኔን ሊታገሡ ይገባል ማለት ነው። ይህ ደግሞ ወገኖች (ወንድሜ ወይም እህቴ) ይታገሳሉ ብለን የጌታን ትዕዛዝ ሁልጊዜ እንጣስ ማለት አይደለም።

**የሰላም ማሰርያ**፡ ሰዎች በአንድነት ሆነው መኖርም ሆነ መስራት የሚችሉት በሰላምና በፍቅር ሲኖሩ ብቻ ነው። ሰላም ማለት ደግሞ ግጭት የሌለበት ሳይሆን ግጭት ወደ ጥል ሳይመራ በፍቅር መፍታት ነው። ሰላም በመሃከላችን ያለውን መንፈስ ቅዱስ ሳይከለከል እንዲሰራ ያደርገዋል።

የመንፈስን አንድነት፡ ይህ ከመንፈስ ቅዱስ የተነሳ ያለንን አንድነት ነው የሚገልፀው።

እርሱ **አንድ** አድርጎናል።

**ኤፌ 4፡4-6 አንድነት፡-** በነዚህ ቁጥሮች ጳውሎስ ቅዱሳንን አንድ የሚያረገንን ነገርና ከዚህም የተነሳ ከላይ በጠቀስው ፍቅር እርስ በርሳችን እንድንተያይ ያሳየናል። ይህ ክፍል የሚነግረን የቅዱሳን አንድነት ያለው በምናመልከው **አንድ አምላክ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ** ነው። አንድ መንፈስ አንድ ጌታ አንድ አባት ነው ያለን። ከዚህ የበለጠ አንድ ሊያደርግ የሚችል ነገር የለም።

**ቁ4."አንድ አካል አንድ መንፈስ"፡** አካል ሲል ቤተክርስቲያንን ነው። መንፈስ ቅዱስም የተሰጠው ለቤተክርስትያን ነው። እኛና እነርሱ ብለን ልንለያይ አይገባም። በሁላችን ያለው የሚሰራ ፀጋውን የሰጠን መንፈስ ቅዱስ አንድ ስለሆነ ነው።

"አንድ ጌታ አንድ እምነት አንዲት ጥምቀት" የሁላችን እምነት ያረፈበት ለሁላችን የሞተ አንድ ጌታ ነው። ጌታም እምነታችንም አይለያይም። የተጠመቅነውም ከእርሱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ ስለሆነ በጥምቀትም አንድ ነን። አንድን ሁለት ማድረግ አንችልም።

**ኤፌ 4፡7-11** በዚህ ክፍል ጌታ ለቤተክርስቲያን ስለሰጣት ልዩ ልዩ ስጦታዎች ይናገራል። ዋና መልዕክቱ ሁላችንም ስጦታ እንዳለንና ስጦው ግን ልዩ ልዩ እንደሆነ ነው። ስጦታውም የተሰጠን ሞቶ በተነሳው ወደ አባቱም ካረገው ከትሳዔው ንጉስ ከጌታ ከኢየሱስ ነው። ቁ 7 ጌታ የአገልግሎት ስጦታ ብቻ ሳይሆን ፀጋንም አብሮ እንደሰጠን ያሳያል። ከቁ 8 እስከ 10 ስለጌታ ኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ ያወራል። ስጦታ ለሁላችን መስጠት የቻለው ጌታ ሞትን አሸንፎ በትንሳኤ ወደስማይ ስለሄደ ነው። ጌታ ወደ ምድር የመጣው በመወለድ ሲሆን ወደ ሰማይ ያረገው ደግሞ ሞትን አሸንፎ በትንሳኤ በመነሳቱ ነው። በዚህ ክፍል የተጠቀሱትን አምስቱን ለቤተክርስቲያን የተሰጣትን ስጦታዎች መዘርዘር አይቻልም።

**ኤፌ 4፡12-13** በነዚህ ቁጥሮች ለቤተክርስቲያን የተሰጡት አገልጋዮችና ስጦታቸው ለምን ምክንያት እንደተሰጡ ዓላማውን ይናገራል። ይህም እርስ በርስ ለመተናነጽ ነው።

"ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ"። እንደ ስሕተት ሽንገላ ባለ ተንኰል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህም እየተንሳፈፍን ሕፃናት መሆን ወደ ፊት አይገባንም፥

**ኤፌ 4፡14-15** ራስ ወደሆነው ወደክርስቶስ ማደግ **በእውነትና በፍቅር** ማደግ ነው። በእውነት እያደግን ስህተትን ማስወገድ አለብን። ያደገ ሰው አንዱን ሰው ከአንዱ መለየት የለበትም።

ኤፌ 4፡16 የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተክርስቲያን ማደግ የምትችለው ሁላችንም የግላችንን ኃላፊነት እየተወጣን ከሌሎች ጋር ደግሞ ተያይዘን ስንኖር ነው። ይህም በፍቅር ብቻ ነው የሚቻለው።

## መደምደሚያ:

ሁሉም ለቤተክርስትያ ጥቅም የእራሱን ድርሻ እየተወጣ ሌሎችም መኖር የፍቅር መገለጫ ነው። የአንድ ወይም የጥቂት ሰው ስራ ቤተክርስቲያንን አያሳድግም። ሁላችን ተያይዘን ስንሰራ ብቻ ነው። "

ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፤ "ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፤ከእርሱም የተነሣ አካል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ፥ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ፥ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል" (ኤፌ 4፡15-16)።

**የመወያያ ጥያቄዎች፡**

1) “ለተጠራችሁበት ጥሪ እንደሚገባ ተመላለሱ” ሲላቸው የተገባው መመላለስ ምን ይመስላል?

ኤፌ 4፡2-3 ላይ ያሉትን ለጥሪያችን ተገቢ የሆኑትን እነዚህን ባህሪያት በዝርዝር ተወያዩበት

2) ኤፌ 4፡4~6 የተገለጠው የቅዱሳን አንድነት ዋናው መሠረቱ ምንድን ነው?

3) ኤፌ 4፡12-13 የተገለጡት የአገልግሎት ግቦች ምን ምንድ ናቸው?

4) ኤፌ 4፡14-15 ላይ ወደ ክርስቶስ ማደግ የሚቻለው በምን በምን ስናድግ ነው? እነዚህን በዝርዝር ተወያዩበት። እውነት እና ፍቅር ከዚህ ጥያቄ ጋር ምን ግንኙነት አለው?

5) ኤፌ 4፡16 ላይ እነደምናየው የክርስቶስ አካል እንዲያድግ ፍቅር እንዴት ይረዳል?

6) የአገልግሎት ስጦታዎቻችሁ ምንድ ነው? እንዴት ልናውቅ እንችላለን? ጌታን የመጀመሪያ ሆኖ ሌሎች ሰዎችን ብናማክርስ? ዛሬም መነጋገር እንችላለን።

7) በቤተክርስቲያን ውስጥ የራሳችንን ተሳትፎ ያላደረግነው ለምን ይመስላችኋል? ከዛሬ በኋላስ እንዴትስ ይህን ችግር ማስወገድ እንችላለን?

# ጥናት ስምንት

በአዲሱ ሰው ማደግ: **4፡17-32**

## **የጥናቱ ዓላማ፡** የአሮጌውን ማንነታችንን እየተውን በአዲሱ ሰው ባህርይ እንድንመላለስ ለማሳሰብ።

## *መግቢያ፡*

ባለፈው ጥናት እያንዳንዳችን ስጦታ እንደተሰጠንና ይህ ስጦታ ደግሞ ቤተክርስቲያንን ወደ ፍጹምነት ለማምጣት እንደሆነ አይተናል። በዚህ ጥናት ይህ ፍጹምነት አሮጌውን ሰው እያሰወገድን አዲሱን በመልበስ የምናድገበት ፍፅምና መሆኑን እናያለን። አሮጌውን ሰው ለማስወገድ አዲሱን ሰው ለመልበስ ስለ ሁለቱም ባህርይ ማወቅ ስላለብን ሐዋርያው ጳውሎስ የአሮጌውንና የአዲሱን ሰው ባህርይ ይዘረዝራል።ራሳችንን የምመዝንበት ሚዛንም ይሆናል።

ኤፌ 4፡17~19 የአሮጌው ሰው ማንነት (9 መለኪያዎች)

በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ለእኛ አሮጌ የምንለው ለማያምኑት ግን አሁንም በእነርሱ ህይወት የሚታይ የአሮጌው ሰው ማንነቶችና ድክመቶች ተዘርዝረዋል። እነዚህም 1) **የአዕምሮ ከንቱነት፡** አዕምሮአችን ቢያውቅም በእውቀቱ አለመኖር፥ እውቀትን ማባከን 2) **አለማወቅ፡-** የሚያውቁትን ባለመጠቀማቸው ከእርነሱ ሲወስድ የመጣ አለማወቅ ነው 3)**የልብ ድንዳኔ፡-** አዕምሮአቸው እየፈረደባቸው ስህተት የሆነውን ለማድረግ መጨከን 4) **የልቡና መጨለም**፡- ከላይ አዕምሮ ከንቱ ሲሆን አዕምሮ ያለእውቀት እንደሚሆን፥ልብ ሲደነድን ልብ ይጨልማል። የሚያውቁት ይወሰዳል። 5) **ከእግዚአብሔር መለየት፡-** ሰው በኃጢአቱ ሲቀጥል ሃጢአት ሞትን ይወልዳል። ይህም የእግዚአብሔርን ህያውነት በህይወታችን እንዳናይ ያደርገናል። 6) **ድንዛዜ**፡- ሃጢአት አድርጎ ፀፀት ሳይሰማ ሲቀር፥ ተግሳፅን አለመስማት።የመፈስ ቅዱስ ወቀሳ ከህይወታችን መራቅስ 7) **ሴሰኝነት፡-** ስጋዊ የሆነ ሰው። ስጋው ያለውን ብቻ የሚያደርግ። 8) **ርኩሰት፡-** ስጋችን የሚፈጽማቸው ሃጢአቶች ናቸው። ሴሰኝነት የሰውየው የውስጥ አመለካከት ሲሆን ርኩስት ያ አመለካከት የሚወልደው ሃጢአት ነው። 9) **ምኞት፡-** የሁሉ ምንጭ የሆነ የዓይን አምሮት ነው።

## *<u>መፍትሔ</u>*

1. **ኤፌ 4፡22~23፡ አሮጌውን ሰው ለማስውገድ ምኞቱንና ሃሳቡን** ማስወገድ አለብን። የአሮጌው ሰው ጉልበቱ ምኞትና ሥጋዊ የአዕምሮ (አስተሳሰብ) ነው ። ስለዚህ በምኞቱ አለመታለልና በአምሮአችን አስተሳሰብ መታደስ አለብን።

   ይህ ክፍል እንደሚከተለው ይላል "ፊተኛ ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ፥በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ፥"

2. **ኤፌ 4፡25 እውነትን መነጋገር፡-** አዲሱን ሰው መለማመድ የሚፈልግ ሁሉ በህይወቱ ያለውን ድካሙን በእውነትና በግልፅነት ለሌላው ማካፈልና ማስወገድ አለበት።

3. **ኤፌ 4፡26~27 በቁጣ አለመቆየት፡-** ተቆጥቶ መቆየት ውስጣችንን በክፉት ሃሳብ እየሞላ ለሰይጣን ፈተና ስለሚያጋልጠን ያስቆጣንን ነገር ቶሎ ከስዎቹ ጋር ተነጋግረን ከልባችን ልናስወጣ ይገባናል። ***"በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፥ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት"*። ስድብ ፤ጩኸት፤**ቁጣ፣ንዴትን፣ ምሬትን መውለድ የለባቸው።**ቁ. 31 ስለዚህ ሂደት ይናገራል *"መራርነትና ንዴት ቁጣም ጩኸትም መሳደብም ሁሉ ከክፋት ሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገድ።"***

4. **ኤፌ 4፡28~29 በተግባር በትጋት በመስራትና ሌሎችን በመርዳት እና በቃልም ሌሎችን**

**ማበረታታት።** ለሌሎች በረከት የሚሆን የህይወት ዓላማ ሊኖረን ያስፈልጋል። "የሰረቀ ከእንግዲህ ወዲህ አይስረቅ፥ ነገር ግን በዚያ ፈንታ ለጎደለው የሚያካፍለው እንዲኖርለት በገዛ እጆቹ መልካምን እየሠራ ይድከም"

**ኤፌ 4፡**30~32 **መንፈስ ቅዱን አታሳዝኑ።** በዚህ ክፍል መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝንና የሚያስደስቱ ነገሮች ተጠቅሰዋል። ቁ31 የሚያሳዝኑት ነገሮች ሲሆኑ ቁ32 ደስ የሚያሰኙት ነገሮች ናቸው። **"የቤዛ ቀን"** ማለት ሰውነታችንን በትንሳኤ በህይወት የሚነሳበትና ከእንግዲህ ወዲህ ሃጢአት የማይሰራና የማይሞት የሚሆንበት ቀን ነው። ይህንም የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ነው።

## መደምደሚያ፡

አዕምሮአችንን በማደስና የሰጋችን ምኞት እንዳያታልለን እየተጠነቀቅን አሮግውን ሰው ማስወገድ አለብን። ለሌሎች ቅዱሳን ግልፅ ሆነን ድካማችንን እየተናገርን የእነሱን ፀሎትና ምክር በመቀበል፥ ቁጣን በቶሎ በማስወገድ በመንፈሳዊ ህይወታችን ያሳድገናል። ዓላማችን ለሌሎች በተግባርም ሆነ በቃል በረከት እንድንሆን ያስፈልጋል። በያንዳንዱ ሰከንድ መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝነውን ነገር በማስወገድ አዲሱን ሰው መልበስ እንችላለን።

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

1) ለእኛ አሮጌ የሆነው ለማያምኑት ግን አሁንም የሚመላለሱበት የአሮጌውን ሰው ችግሮች ደረጃ በደረጃ ኤፌ 4፡17~19 ተገልፆአል። እነዚህን 9 የሚደርሱትን ችግሮች ጊዜ ወስዳችሁ በዝርዝር ተወያዩበት።

2) እራሳችንን በነዚህ በአሮጌው ሰው መስፈርቶች ስናይ፤በእኛስ የሚታዩ ድክመቶች አሉ?

3) **ኤፌ 4፡**22-23 መሰረት የአሮጌው ሰው ጉልበቱ ያለው የት ነው? ሐዋርያው ጳውሎስ ምን ያዘናል?

4) **ኤፌ 4፡**25 ላይ እርስ በእርስ መነጋገር ያለብን እውነት ምንድን ነው? ለምንድን ነው እውነት መነጋገር ያለብን?

## ***<u>የዛሬው ጊዜ ካልበቃችሁ ከዚህ በታች ያለትን ጥያቄዎች በሚቀጥለው ቀን ማጥናት ትችላላችሁ</u>***

5) ዲያቢሎስ እድል ፈንታ የሚያገኘው መቼ ነው? እንዴት ነው ዕድል ፈንታ አለመስጠት የሚቻለው?

6) **ኤፌ 4፡**28እና 29 መሰረት ሊኖረን የሚገባ ዓላማ ምንድን ነው?

1) “የቤዛ ቀን” ሲል ምን ማለቱ ነው? መቼ ነው ያ ቀን? በዚህ ክፍልስ እንዳናደርግ የታዘዝነው ምንድ ነው?

2) መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝኑትን ነገሮችን ተወያዩበት?

3) **ኤፌ 4፡**32 መሰረት መንፈስ ቅዱስን በሚያሳዝኑት ነገሮች ምትክ ምን እንድናደርግ ታዘናል?

4) አሮጌውን ማንነታችንን እያስወገድን አዲሱን እየለበሰን ለመኖር እየተጋን ነው? በዚህ ትግል ላይ ያለን የፀሎት ርዕስ ተለዋውጠን እንፀልይ

# ጥናት ዘጠኝ

## በፍቅር ተመላለሱ

ክፍል አንድ፡ ፍቅር ለእግዚአብሔር: 5፡1-20

## የጥናቱ ዓላማ፡

ክርስቶስ እኛን እንደወደደን እርሱን በመውደድ የእርሱን አርአያ እንድንከተል ለማሳሰብ።

## መግቢያ፡

ባለፈው ጥናት የአዲሱን ሰው ባህርይ እንዴት መልበስ እንዳለብን አይተናል። በዚህ ጥናት ደግሞ አንዱና ዋነኛ የሆነውን <u>የአዲሱን ሰው ባህርይ እርሱም ፍቅርን</u> እናያለን። ክርስቶስ እኛን ወዶ ስለሞተልን እንድናምነው ብቻ ሳይሆን አርአያውን እንድንከተል ይፈልጋል። የእርሱን ምሳሌ የምንከተለው ራሱን በምንወድበት ፍቅር ነው። እርሱ ራሱን መስዋዕት አድርጎ እንደሰጠን እኛ ደግሞ ራሳችንን መስዋዕት አድርገን ለእርሱ በማቅረብ ልንወደው ይገባል። "እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ፥ክርስቶስም ደግሞ እንደ ወደዳችሁ ለእግዚአብሔርም የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባንና መሥዋዕትን አድርጎ ስለ እናንተ ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ በፍቅር ተመላለሱ" (ኤፌ 5፡1) ። ይህ ክፍል ከኤፌ5፡25-32 ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለው።

**ኤፌ 5፡**1-2"እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ፥

ክርስቶስም ደግሞ እንደ ወደዳችሁ ለእግዚአብሔርም የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባንና መሥዋዕትን አድርጎ ስለ እናንተ ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ በፍቅር ተመላለሱ"። **"እንደተወደዱ ልጆች"** ሲል እግዚአብሔር እኛን ልጆቹ እንዳደረገንና እንደወደደን ለማሳየት ነው። "እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ" ሲል የፍቅራችን ምሳሌ ክርስቶስን ይነግረናል።

**ኤፌ 5፡**3-4 **ለቅዱሳን የሚገባና የማይገባው ነገር፡-** በነዚህ ቁጥሮች የተገለጠውን ለቅዱሳን የሚገባና የማይገባው አኗኗር ምን እንደሚመስል እናያለን "ለቅዱሳን እንደሚገባ ግን ዝሙትና ርኵሰት ሁሉ ወይም መመኘት በእናንተ ዘንድ ከቶ አይሰማ። የሚያሳፍር ነገርም የስንፍና ንግግርም ወይም ዋዛ የማይገቡ ናቸውና አይሁኑ፥ ይልቁን ምስጋና እንጂ"። እዚህ ጋር ጳውሎስ ሃጢያትን አይገባኝም ብለን ከህይወታችን እንድናስወግደው ያስረዳናል። "አይገባም" "የሚያሳፍር" የሚሉት ቃላት በህይወታችን ከመጣው ለውጥ የተነሳ (በደሙ ስለታጠብን) ሃጢያት እንዳያቆሸሸን መተው አለብን።

**ስኤፌ 5፡5-6 በኃጢአት ብንቀጥልስ?** በነዚህ ቁጥሮች ደግሞ ሃጢአትን አማኝ መስራት እንደሌለበት ይናገራል። አይገባኝም ብለን ማቆም ካቃተን ቅጣት አለው ብለን እንድናቆም ነው። ሃጢያት የእግዚአብሔርን መንግስት በሙላት እንዳናይ ያደርጋል።

**ኤፌ 5፡7-13 በንጽህና ለመኖር ከማን እንራቅ (ህብረታችን)?** ሃጢያትን ማቆም ብቻ ሳይሆን ሃጢያት ከሚያደርጉ ወይም ከሚያዘውትሩ ሰዎች ጋር ሃጢያትን የማድረግ እድል እንዳይገጥመን ህብረት ማድረግ የለብንም። ደግሞም የብርሃን ልጆች እንደመሆናችን ሃጢያት መሆኑኑ ማሳየት አለብን።

**ኤፌ 5፡15-20 ታዲያ እንዴት እንኑር?** እነዚህ ቁጥሮች ቅዱሳን ክፉ በሆነው በዚህ ዘመን ሃጢያትን ሳያደርጉ እግዚአብሔርን በመውደድ እንዴት መመላለስ እንደሚችሉ ያሳያሉ። እርሱም በጥበብ መኖር ነው። ጥበበኛ ሰው ነገሮችን መጠቀም የሚችል ነው። ስለዚህ ጥበበኛ አማኝ ክፉ ሲደርስበት በጥበብ ለጥቅሙ ማዋል ይችላል (ሁሉን ለበጎ መጠቀም ማለት ነው)። ይህ የሚቻለው በክፉ ነገር ውስጥ እንኳ የእግዚአሕብር ፈቃድ ምን እንደሆነ ማወቅ ሲቻል ነው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ሊያሳውቀን በውስጣችን ስላለ በእርሱ ውስጣችንን

መሙላት ማለትም ለእርሱ መገዛት አለብን። ክፉውን ግን በመጠጥና በስካር ለመሸሽ ግን መሞከር የለብንም። በዝማሬ እርስ በርሳችን እየተበረታታን ክፉውን ዘመን ለማለፍ መጣር አለብን። እግዚአብሔርንም በክፉው በማንኛውም ሁኔታ እንኳ ልናመሰግነው ይገባል።

## መደምደሚያ፡-

ኤፌ 5፡1-2 "እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ፥ክርስቶስም ደግሞ እንደ ወደዳችሁ ለእግዚአብሔርም የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባንና መሥዋዕትን አድርጎ ስለ እናንተ ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ በፍቅር ተመላለሱ"።በብርሃን እንዳለ ሰው ነውር የሌለበትን ኑሮ በመኖርና በተለይ ደግሞ ክፉ የሆነ ጊዜ በህይወታችን ሲመጣ ሃጢያትን ከማድረግ ይልቅ ለጌታ ያለንን ፍቅር የምንገልጥበት አጋጣሚ አድርገን ልንጠቀምበት ይገባል። ክፉውን ጊዜ ለግል ጥቅማችን ለጌታ ክብር ማድረግ የምንችለው በመንፈስቅዱስ እርዳታ ጌታ ለምን ክፉውን እንደፈቀደ ለማወቅ ስንጥርና እርስ በርሳችሁን ስንበረታታ ጌታንም በማመስገን ህይወት ስንተጋ ነው።

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

1) **ኤፌ 5**፡1-2 መሰረት እግዚአብሔርን መከተል ማለት ምንድን ነው ወይም በምንድን ነው የምንከተለው? ክፍሉስ የምንከተልበትን ምክንያት ምን ይለዋል?

2) **ኤፌ 5**፡3-6 ድረስ ለቅዱሳን የሚገቡና የማይገቡ ባህርያት ተገልፀዋል። እነዚህን ተወያዩባቸው። በዚህ ዘመን ላለን ክርስትያኖች ብዙ ጊዜ አስቸጋሪ የሆኑትን አስረዱ።

3) **ኤፌ 5**፡7-13 ድረስ በብርሃንና በጨለማ ያሉ ሰዎች ልዩነት እንዴት ነው የተገለፀው?

4) ኤፌ 5፡15 "እንግዲህ እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ" ጥበበኛና ጥበብ የሌለውን ሰው ኑሮ በማነፃፀር ተወያዩ። ማን ነው ጥበበኛ? መለኪያውስ ምንድ ነው?

### *<u>የዛሬው ጊዜ ካልበቃችሁ ከዚህ በታች ያለትን ጥያቄዎች በሚቀጥለው ቀን ማጥናት ትችላላችሁ</u>*

5) **ኤፌ 5፡16 "ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ"** ሲል ምን ማለቱ ነው? መልካም ሲሆንልን ብቻ ሳይሆን ክፉም ሲሆን ጌታ ሁሉንም ለመልካም መለወት እንደሚችል አውቀን ዘመኑን እግዚአብሔር እኛን ለጠራበት ዓላማ መጠቀም መቻል ማለት ነው ወይስ ሌላ?

6) ክፉ ዘመን ነው ብለን ተስፋ ቆርጠን እጃችንን አጣምረን መቀመጥ አለብን ወይስ የለብንም? ሁሉን በጎ ከሚያደርግ ጌታ ጋር ስለምንኖር ዘመናችንን ለጌታ አሳልፈን እየሰጠን መዋጀት/ለእኛ ጥቅሙ ምንድ ነው?

7) ኤፌ 5፡17 የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ ማስተዋል ዘመኑን ለመዋጀት ምን ይጠቅማል?

8) **ኤፌ 5፡**18-20 ድረስ ክፉውን ቀናት መዋጀት የምንችልባቸው መፍትሄዎች ምን ምን ናቸው? እያንዳንዱ እንዴት ቀኑን ለመዋጀት እንደሚረዱ ተወያዩበት። ይህ ሀሳብ ከመጠጥና ከመስከር ጋር ምን ይገናኛል?

9) ኤፌ 5፡18-19 በመንፈስ ቅዱስ መሞላት፣ መዘመርና ማመስገን ከጠቅላላ ሀሳብ ጋር ምን ግንኙነት አለው?

10) ለጌታ ያለንን ፍቅራችንን እንዴት ነው በግላችሁ የምንገልጠው? ክፉት በህይወታችን ሲመጣ ለጌታ ያለንን ፍቅር ይቀንሳል ወይስ ይቀጥላል?

# ጥናት አስር

## በፍቅር ተመላለሱ፡

## ሁለት፡

ፍቅር ለእርስ በእርስ (በቅርብ አብረው ለሚኖሩ ሁሉ)፡ 5፡21~33

## የጥናቱ ዓላማ፡-

ክርስቶስ ያሳየንን ፍቅር ለእርስ በርሳችህን ማሳየት እንድንችል ለማበረታታት።

## መግቢያ፡

ባለፈው ጥናት ክርስቶስ በወደደን ፍቅር እሱን ወደን የእርሱን ትምህርት መከተል እንዳለብን አይተናል። በዚህ ጥናት ደግሞ ያንን ፍቅር ከእኛ ጋር ህብረት ለሚያደርጉ ሁሉ በመገዛትና እነሱን በፍቅርን በመንከባከብ የክርስቶስን ሕይወት መከተል እንዳለብን እናያለን። በግላችን ብቻ ሳይሆን እንደቤተክርስቲያንም በአንድነት ለክርስቶስ ልንገዛና እሱ ለእኛ የሆነልንን ሁሉ ልናስተውል እንደሚገባን እናያለን። ሁሉ ሰው ስለ ክርስቶስ ብሎ ሰውን እንዲወድ ይጠይቃል።

ትልቅ ትህትናና ራስን መግዛት የሚጠይቅ ክፍል ነው።

**ኤፌ 5፡21፦ ቀጥሎ ላሉት ትምህርቶች መሰረታዊ ነገር** ነው። **"ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ"** የሰው ልጅ ስለ ክርስቶስ ፍርሃት ሁሉን እንዲያደርግ ይጠይቃል ። የግል መብታችንን ለማስጠበቅ ከመታገል ይልቅ የሌላውን ፈቃድ ለማድረግና መብት ለመጠበቅ መታገል እንዳለብን ያሳያል።

**ኤፌ 5፡22~24 ሚስት ለባልዋ መገዛት ያለባት ለጌታ እንደምትገዛው ነው።** ለጌታ ስትገዛ መገዛትዋ ለጥቅሙዋ እንደሆነ አውቃ እንደሆነ፥ እንዲሁ ለባልዋ መገዛት ስለሚጠቅማት እንጂ ለመጨቆን አይደለም። ቤተክርስቲያን ለጌታ ስትገዛ ብቻ ነው ጌታ ለእርሷ የሚያደርገውን በረከት ማየት የምትችለው። እንዲሁም ሚስት ለባል ስትገዛ ባልየው ለእርሷ የበለጠ እንዲያስብና እንዲኖር ያደርገዋል። ኃላፊነት ይሰማዋል።

**ኤፌ 5፡25~27 ባሎች ሚስቶቻቸውን መውደድና መንከባከብ ያለባቸው ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደደና እንደተንከባከበ ነው።** ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን የከፈለው ዋጋ ለራሱ ብሎ እንደነበር ባሎችም ለሚስቶቻቸው ዋጋ ሲከፍሉ ተጠቃሚዎቹ ራሳቸው ባሎች እንድሆኑ ሊያስቡ ይገባል።

**ኤፌ 5፡28~33 ባሎች ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን ያለውን ፍቅር ከማየት በተጨማሪ ራሳቸው የገዛ ስጋቸውን እንዴት እንደሚወዱ አይተው ሚስቶቻቸውን እንደ ገዛ ስጋቸው መውደድና መንከባከብ አለባቸው።** ባል እናቱንና አባቱ ትቶ ከሚስት ጋር በመተባበር ከእርሷ ጋር አንድ ስጋ ስለሆነ ስጋዬ ነች ብሎ መውደድ አለበት።

**መደምደሚያ፡- ኤፌ 5፡21 የጠቅላላ ሀሳብ መሪ መልዕክት ነው። ስለዚህ አንድ ሰው ኤፌ 5፡21ን ሥራ ላይ ካዋለ ሌላውን መታዘዝ አይከብደውም።** እንደ ቤተክርስቲያን ሁላችን ክርስቶስ እንዴት እንደወደደን አውቀን ለእርሱ ልንገዛ፥እንዲሁም ለእርስ በእርሳችን ስለጌታ ብለን ልንገዛና ያገባን ከሆንን ደግሞ የቤተክርስቲያንና የክርስቶስን ህብረት ምሳሌ ያደረገ የትዳር ግንኙነት ልኖረን ይገባናል። ያላገባንም የክርስቶስን የፍቅሩን ምሳሌ ተከትለን የወደፊት ህይወታችንን ማለም አለብን።

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

1) **ኤፌ 5፡21** ለሚቀጥሉት ቁጥሮች መሪ ሀሳብ ነው። ለምንድ ነው እንደ መሪ ሀሳብ የሚጠቅመው?

2) **የጌታን ቃል ዛሬም ያሉ ባለትዳሮች ለራሳቸው ጥቅም እንዴት እንደሚያጣምሙ ተነጋገሩ (ለምሳሌ መገዛት…)** መፍትሔውስ ምንድ ነው?

3) **ኤፌ 5፡22-24** የሚስቶች ለባሎቻቸው መገዛትና ቤተክርስቲያን (ሚስትንም ባልንም ይጨምራል) ለጌታ መገዛት እያነፃፀራችሁ ሚስት ለባል መገዛት አለባት የሚለውን ተወያዩበት።

4) **ኤፌ 5፡25-30** ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን የወደደበትን ፍቅርና ባሎች ሚስቶችን ሊወዱበት የሚገባውን ፍቅር አነፃፅሩና። ባሎች ሚስቶችን እንዴት ሊወዱ እንደሚገባ ተነጋገሩ።

5) ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን የሆነውና ያደረገው ያቀደው ምን ምንድን ነው? ይህ በህይወታችሁ ሆኖአል ደግሞስ እየሆነ ነው?

6) ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል ማለት ምን ማለት ነው? ለራሱ የሚወደውን ነገር እንድትሆንለት ወይም እንድታደርግ ቢደከምላት ይህ ዓይነቱ ፍቅር ሚስትን መውደድ ነው?

7) ጳውሎስ በዚህ ክፍል ስለቤተክርስቲያንና ስለክርስቶስ ህብረት ያወራው በቤተክርስቲያናችን እውነት ሆኖ ታዩታላችሁ? ካልሆነ እያንዳንዳችሁ ያልሆነበትን ምክንያት ከግል ችግራችሁ ጀምራችሁ ከነመፍትሄው ተወያዩበት።

8) የዛሬው ጥናት ላላገቡት ምን ትምህርት አለው?

9) ያገባችሁ ሰዎች ራሳችሁን በዚህ ክፍል መሰረት ስታዩት ማስተካከል የሚትፈልጉትን ጉዳይ ፈቃደኞች ከሆናችሁ ለህብረቱ ወይም ለምታምኑት ሰው ተናግራችሁ ይፀለይላችሁ።

# ጥናት አሥራ አንድ

(ጊዜው ካልበቃችሁ የሁለት ቀን ጥናት ይሁን)

ክርስቲያን የጌታን ኑሮ ከቅርብ ቤተሰብ ጀምሮ የመኖር ኃላፊነት አለበት: **ኤፌ 6፡1-9**

## ዓላማ፡-

ቤተሰብ ወይም ጌታና ባርያ (ሰሪና አሰሪ) የጌታን ትዕዛዝ እየጠበቁ መኖር ሰላም ያመጣል። ስለዚህ ይህ የማንኛውም ክርስቲያን ኃላፊነት መሆኑን ማሳወቅ

## መግቢያ፡-

በርግጥ ይህ ክፍል ብቻውን የቆመ ክፍል ሳይሆን ከኤፈሶን 5፡21-33 ካለው ክፍል የቀጠለ ነው። በተለይም ኤፌ5፡ 21 ሊሰመርበት የሚገባ ክፍል ነው። ክፍሉም በሰው መካካል ስላለው ስለ እርስ በርስ ክርስቲያናዊ ግንኙነት መለኪያ ይናገራል። በዚህ ክፍል በአራት ዓይነት ሰዎች መካካል ሰላለው የግንኙነት ሥነ ምግባር ማለትም በልጆች፣ በወላጆች፣በጌቶችና በባሪያዎች፣ መካካል ስላለው ክርስቲያናዊ የሥነ ምግባር ግንኙነትና ማለት ነው። ያልዳነ ወይንም ሥጋዊ ክርስቲያን ባህሪይ ያለው ሰው አህዛብና አይሁድ በመሆን ብቻ ሳይሆን እርስ በርስ ቤተሰብ ውስጥም አብሮ የመኖር ችግር ልኖር ይችላል። ስለዚህ ሐዋ ጳውሎስ ይህን ችግር ለማስወገድ ያስተምራል።

## 1. ወላጆችና ልጆች- ኤፌ 6፡1-4፡

ሐዋ ጳውሎስ ይህን ክፍል የቀጠለው የባልና የሚስት በጋብቻ መካከል ስላለው ክርስቲያናው ኃላፊነት በምዕራፍ አምስት ከተናገረ በኋላ ነው። ወላጆችና ልጆችም ደግሞ እርስ በርስ የጌታን ቃል በመጠበቅ እንደዚሁ መኖር ይጠበቅባቸዋል (ኤፌ 5፡21ን በቃላችን እናብብ)።

## ኤፌ 6፡1-3 ልጆች ለወላጆች መታዘዝ ያለባቸውንም አራት ምክንያቶችን ያቀርባል

**1. በጌታ ስለሆኑ (ቁ.1)**፡- ይህ ትዕዛዝ ከምዕራፍ 5፡21 ጀምሮ ያለውና የተያያዘ መሪ ሃሳብ ነው (**"ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ"**)። ቆላ 3፡1-25 ሙሉ ቢነበብ መልዕክቱን ያጠነክራል። ሰው ሁሉ የሚያደርገውን ጌታ እያሰበ የሚደርግ ከሆነ መታዘዝ አይከብደውም

**2. ተገቢ ስለሆነ "...ይህ ተገቢ ነው"**፡- ምን ብለን መጠየቅ እንችላለን።ልጆች ለወላጆች መታዘዝ በተፈጥሮ እግዚአብሔር ካስቀመጣቸው ህጎች አንዱ ነው። አለመታዘዝ ቢኖር በተፈጥሮ ያለውን የእግዚአብሔርን ህግ መጣስ ነው። ሰው ለተፈጥሮና ለህልና ህግ ተጠያቂ ነው (ሮሜ 1)። እግዚአብሔር በተፈጥሮ ያስቀመጣቸውን ብዙ የተፈጥሮ ህጎችን ማሰብ እንችላለን (የመሬት የጸሐይና የጨረቃ ግንኙነትና ሌሎችም)።

**3. ፊተኛይቱ ትዕዛዝ ስለሆነች፡- "የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት"?** ይህ ሀሳብ ያለው በዘጸ 20፡5 ሆኖ አምስተኛው ትዕዛዝ ነው። በአዲስ ኪዳን ሰንበትን ስለመቀደስ ካልሆነ በስተቀር ሁሉም አስርቱ ትዕዛዛት ከብሉይ ኪዳን ተደግመዋል ወይም ተብራርቷል። ግን በዚህ ክፍል ደግሞ የሚታዘዙትም ወይም መታዘዝ ያለብንም ለጌታ እየታዘዝን እንደሆነን በመገንዘብ ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ ፍቅር ሕግን ሁሉ ይፈጽማል "ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም፤ ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው" (ሮሜ 13፡10)። መታዘዝ በአፍ እሺ ከማለት ያለፈ የተግባርና የፍቅር ኑሮ ነው። ሉቃ 2፡51፣ዕብ 5፡8 በማንበብ ከጌታ ህይወት መማር ይቻላል። ሰለ ጌታም እንዲህ ይላል "ከእነርሱም ጋር ወርዶ ወደ ናዝሬት መጣ፥ ይታዘዝላቸውም ነበር" (ሉቃ 2፡51)።

**4. የበረከት አንዱ መንገድ ስለሆነ፡- "መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም".** በዚህ ክፍል ደግሞ ሰው ወላጆቹን በመታዘዝ የሚያገኘውን በረከት ያመለክታል። ይህም ደግሞ በዘጸ 20፡12 ላይ ከአሥርቱ

ትዕዛዛት ለአምስተኛው ትዕዛዝ እንደ ውጤት የሚናገር ክፍል ነው። ከጌታ የሚገኙ በረከቶች መልካም ናቸው። ብዙ ዓመት መኖር ማለት ምን ማለት ነው? በምድር ላይ መቶ እና ከዚያ በላይ መኖር ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። ጥቂት ዓመታትን በእግዚአብሔር ቤት በእርሱ ህልዎትና ወላጆችን በመታዘዝ በሰላም መኖር በረከት ነው። **መንፈሳዊ ፍሬ በማፍራት ወላጆቻችንን ማክበር አለብን።**

## 2. የወላጆች ኃላፊነት: ኤፌ 6፡4

በዚህ ክፍል መሰረት ወላጆች ልጆቻችንን በሁለት ነገር እንድናሳድጋቸው ይጠብቅብናል።፡ 1. **በጌታ ምክር፦** የጌታ ምክር በጌታ ቃል ስለሚገኝ ድነት እና ሥነ ምግባር ማስተማርን ይመለከታል። ይህ ደግሞ በሙሉ ሁለንተና ማለትም በሥጋ በነፍስና በመንፈስ ማሳደግን ይጠይቃል። በጌታ ቤትም የማገልገል ኃላፊነት እንዳለባቸውም ያመለክታል። ኃለፊነት የሚሰማቸው ጥሩ የሀገር ዜጎችም የማድረግ ኃላፊነት አለብን። 2. **"በተግሣጽ አሳድጉአቸው"**፦ ዕብ 12፡6 ጥሩ ማስረጃ ይሆናል። ምሳ 13፡24 "በበትር ከመምታት የሚራራ ሰው ልጁን ይጠላል ልጁን የሚወድድ ግን ተግቶ ይገሥጻዋል"። በበትር ማሳደግ በስሜታዊነት የሚደረግ ነገር ሳይሆን በዓላማና በትዕግስት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ብቻ የሚደረግ ነገር ነው። መነጋገር ለሚችሉ ዓላማውም ለልጆች መብራራት አለበት። ፍቅራችንን እንዳይገድል ማስተዋልና መጠንቀቅ አለብን።

## 3. ባሪያዎችና ጌቶችኤፌ 6፡5-8

**"ባሪያዎች ሆይ፥ ለክርስቶስ እንደምትታዘዙ** [ይህ ዋናና መሪ ሃሳብ ነው]...ለሥጋ ጌቶቻችሁ..." **ኤፌ 6፡5** ቀጥሎ ያለው የባሪያዎችና የጌቶች ወይም በአሁን ዘመን ንግግር በተለያየ ደረጃ ያሉትን የአሰሪዎችና ሰራተኞች ክርስቲያናዊ የአስተዳደር ሥርዓትና ህብረት በወንጌል ነጻነት ምን እንደሚመስል ይናገራል። በርግጥ በአንዳንድ ህብረተሰብ ጌቶችና ባሮች አሁንም አሉ። መስፈርቶችስ ምንድ ናቸው?

1. በፍርሃት
2. በመንቀጥቀጥ
3. በልብ ቅንነት
4. ለጌታ እንደሚገዙ በማሰብ
5. በትጋትና በበጎ ፈቃድ በማድረግ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚያደርጉ በማሰብ ማድረግ አለባቸው ይላል። የዚህ ውጤት ቁ.8 ላይ ተጠቅሳል "ከጌታ በብድራት እንዲቀበለው ታውቃላችሁና"።

ብዙዎች እንደሚሉት በጊዜው ወደ 6 ሚሊዮን የሚሆኑ ባሪያዎች በሮማዊያን ግዛት ይኖሩ እንደነበር ይነገራል። ብዙ ይጨቆኑም ነበር። ክርስቲናን መቀበላቸው ሌላ ተጨማሪ ችግር የሚያመጣ ነገር ነው። ምክንያቱም "ክርስቲያን ከሆንክ ነጻ ነህ ማለትም በሥጋም ቢሆን በሥራና በተመሳሳይ ነገሮች ለሌላው ሰው ተገዝቶ መኖር አያስፈልግም" ብለው የሚያውጁም ነበሩ። ይህ ትምህርት በርግጥ ትክክለኛ አልነበረም።ባሉበት ሆኖ በጌታ መለወጥና ለሰው ተገዝቶ መኖር ማለት ምን ማለት እንደሆነ መንፈሳዊ እውቀትን ማወቅ አስፈላጊ ነው። ለነዚህም ጥበብ በተሞላ መንገድ ማስተማር ነበረበት። ወንጌል ሰውን በግድ ሳይሆን በፍቅር እርስ በርስ መከባበር እንዲችሉ ኃይል መስጠት ነው።ቲቶ 2፡9-10 "ባሪያዎች ስለ መድኃኒታችን ስለ እግዚአብሔር የሚሆነውን ትምህርት በሁሉ ነገር ያስመሰግኑ ዘንድ፥ ለገዛ ጌቶቻቸው እንዲገዙ በሁሉም ደስ እንዲያሰኙ፥ ሳይቃወሙና ሳይሰርቁም በጎ ታማኝነትን ሁሉ እንዲያሳዩ ምከራቸው"። ክርስቶስ ሲሰበክ የሰውን ሁለንተና (አእምሮ፣ፈቃድና ዕውቀት) ይቀይራል፤ያስገዛል (ሮሜ 12፡1 1ተስ 5፡23)። ሥጋዊ የሆነ የገዥና የተገገርን አሉታዊ አስተሳሰብ ይቀየራል። ሁሉም

ስለ ጌታ መኖር ይጀምራል። ወንጌል የሥልጣን ክፍፍልን አይቃወምም። ከጌታ ቃልና ከተፈጥሮም ይህንን ማየት ይቻላል።

6፡9 **ጌቶች ከባሮች የሚፋልጉትን እነርሱም ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡-** አሰሪዎች ከሰሪዎቻቸው መልካም ነገርን የሚጠብቁ ከሆነ እንደዚሁ ለጌታ ብለው ለባሮቻቸው ወይም ለሰራተኞቻቸው መልካም ነገርን ማድረግ አለባቸው። በጌታ ከተለወጠ ጌታ ወይም አሰሪ ሌላውን መበዝበዝና ማንቋሸሽ አይጠበቅበትም። ይህን ሁለቱም ክፍል ካደረጉ ለራሳቸው፣ ለሰውና ለጌታም መልካም ስምና ምስክርነት ይሆናል። እንዲህ ከሆነ ሁሉም ለእግዚአብሔር ክብር ይሰራሉ ("እነሆም፥ ቦዔዝ ከቤተልሔም መጣ፥ አጫጆችንም "እግዚአብሔር **ከእናንተ ጋር ይሁን** አላቸው" እነርሱም፡- **እግዚአብሔር ይባርክህ ብለው** መለሱለት" (ሩት 2፡4)። ይህ ጥሩ ምሳሌ ነው። ዮሴፍ፣ሙሴ፣ኢያሱ፣ዳዊት፣ዳንኤል፣ነህምያ በሰው ሥልጣን ሥር ይሰሩ ነበሩ። ሁሉም ስለ ጌታ ያለበትን ኃላፊነተ መወጣት አለበት።

## መደምደሚያ፡-

እንደሚታወቀው በብዙ ክርስቲያኖች መካካል ለጌታ ብሎ እርስ በርስ የመገዛት መርህ ስለሚጣስ ቤተሰብ፣ጌቶችና ባሮች ወይም አሰሪና ሰራተኞች መካከል አብሮ መኖር እየቀነሰ ይገኛል። ይህንን ችግር በክርስቲያናዊ ስነ ምግባር የጌታን ኑሮ እየኖሩ ማስወገድ ይቻላል። ሰላምም ያለው በወንጌል ነው። ሁሉም ለጌታ ከተገዛ እርስ በርስ አብሮ መኖር አይከብድም።

ቲቶ 2፡9-10 "ባሪያዎች ስለ መድኃኒታችን ስለ እግዚአብሔር የሚሆነውን ትምህርት በሁሉ ነገር ያስመሰግኑ ዘንድ፥ ለገዛ ጌቶቻቸው እንዲገዙ በሁሉም ደስ እንዲያሰኙ፥ ሳይቃወሙና ሳይሰርቁም በጎ ታማኝነትን ሁሉ እንዲያሳዩ ምከራቸው"።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1) ልጆች ለወላጆች መታዘዝ ያለባቸውን አራት ምክንያቶችን ጠቅሳችሁ ተወያዩ (**ኤፌ 6፡1-3**)

2) ልጆች ለወላጆች መታዘዝ የተገባ ነው የሚለውን መልዕክት አብራሩ (**ኤፌ 6፡1-3**)። በተጨማሪ ልጆች ለወላጆች መታዘዝ መባረከ ነው ማለት ምን ማለት ነው (200 ዓመት በምድር መኖር ነው?)

3) ምሳ 13፡24 "በበትር ከመምታት የሚራራ ሰው ልጁን ይጠላል ልጁን የሚወድድ ግን ተግቶ ይገሥጻዋል" ይህን ሀሳብ ካለንበት ሀገር ሥልጣኔ፣ ባህልና ህግ ጋር እንዴት እናስታርቃለን?

4) በ1ቆሮ 7፡20 "እያንዳንዱ በተጠራበት መጠራት እንደዚሁ ይኑር" የሚለው ሃሳብ ከባሮችና ጌቶች ግንኙነት ጋር ምን ይገናኛል?

5) ሩት 2፡1-4 እናብብ "እነሆም፥ ቦዔዝ ከቤተ ልሔም መጣ፥ አጫጆችንም። እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን አላቸው። እነርሱም፦ "እግዚአብሔር ይባርክህ ብለው መለሱለት" (ሩት 2፡4) ይህ ቃል ከባርሮችና እና ከጌቶች አስተዳደር ጋር እንደ ጌታ ሰዎች ምን ትርጉም አለው? ተወያዩ። የክርስቲያን ባሪያ ወይም ሰራተኛ ኃላፊነቶችን እናብራራ።

6) ዛሬ ምን ተማርን? ከበላያችን ላሉት መሪዎቻችን ወይም አለቆቻችን እንዴት ነው እየተገዛን ያለነው? አለቆችስ ወይም መሪዎች ከሆነን እንዴት ነው የምንገዛቸው?

# ጥናት አሥራ ሁለት

የእግዚአብር የጦር ዕቃ (መንፈሳዊ ውጊያ) እንደ ክርስቲያን አብሮ ለመኖር ትልቅ ዋጋ አለው፡
ኤፌ 6፡10-24

## ዓላማ፡-

እግዚአብሔር ለአይሁድም ሆነ ለአህዛብ በጸጋ ያዘጋጀውን ድነት ለመጠበቅ መንፈሳዊ ውጊያ ትልቅ ቦታ እንዳለው ማሳወቅ

## መግቢያ፡-

ሐዋ ጳውሎስ የሐዋ ሥራ 19፡21-41 ሲነበብ በኤፌሶን ከተማ በወንጌል ሥራው ከባድ ተቃውሞ (መንፈሳዊ ውጊያ) ገጥሞት እንደነበር ይታወቃል። በኤፌሶን ያገለግል ለነበር መጋቢ ጢሞቴዎስ የወታደር መርህ ጽፏል (1ጢሞ 6፡12 እና 2ጢሞ2፡3-4)። ይህ ክፍል ክርስቲና አንዳንዶች እንደሚሉት የመደሰቻ ሜዳ ብቻ ሳይሆን የውጊያም እንደሆነ ይነግረናል። ውጊያውም ደግሞ መንፈሳዊ ነው። በዚህ ክፍል ሐዋ ጳውሎስ አንድ የሮማዊ ወታደር ስዕላዊ መግላጫ ይጠቀማል። በርግጥ በወቅቱ እርሱም በሮማዊያን ወታደሮች ቁጥጥር ሥር በሮም ከተማ እንደነበረ ግልጽ ነው።ከፋ የሰዎችን ድነት ስለማይፈልግ ለመጣል እንደገና የጥል ግድግዳ ለመፍጠር ጥረት ያደርጋል። ስለዚህም መንፈሳዊ ውጊያ አብሮ ለመኖር መሰረታዊ መርህ ነው። የጦር ዕቃዎቹም መንፈሳዊ ናቸው። ለውጊያውም የኃይሉ ምንጭ ጌታ መንፈስ ቅዱስ ነው።

**ኤፌ 6፡10-12 እርስ በርስ አብሮ ለመኖር በጌታ ኃይል ንቁ መሆን አለብን**

ኤፌ 6፡10 "**በቀረውስ** በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ"፡- ይህ ሃሳብ የሽግግር ንግግር ነው፤ማለትም ከላይ እርስ በርስ በጌታ ስላለው ህብረት አይሁድም ሆነ አህዛብ፣በቤተሰብም ሆነ በባሮችና በጌቶችም መካከል ላለው ክርስቲያናዊ ህብረት ተቃዋሚ መንፈስ እንዳለ አውቆ በጌታና በእርሱ ኃይል ብርቱዎች (ንቁዎች) መሆን እንዳለባቸው ይመክራል።

የጸሎቱ ሂዳት፡-

**ኤፌ 6፡11 ከውጊያው በፊት ልብስ መለበስ አለበት**፡- መንፈሳዊ ውጊያ የሚደረገው በራሳችን ችሎታና ኃይል አይደለም ነገር ግን በእግዚአብሔር ዕቃ ጦር ሆኖ ለብሶ መዘጋጀት የክርስቲያን ኃላፊነት ነው። ልብሶቹን ከቁ13 በኋላ እናያቸዋለን። ውጊያውም የሚካሄደው መሰረትና እውነት ካለበት ነገር ጋር ሳይሆን የዲያብሎስን ሽንገላና ክስ ለመቃወም ነው። ዲያብሎስ ትርጉሙ ከሳሽ ማለት ሲሆን ሰይጣን ማለት ደግሞ ጠላት ወይም ተቃዋሚ ማለት ነው። እርሱ ፈታኝና ነፍስ ገዳይ ሐሰተኛ ነው (ማቴ 4፡3፣ዮሐ 8፡44)። ብዙዎችን በማታለልና ነፍስ በመግደል ላይ ይገኛል። ሌባም እንደሆነ ጌታ ስለ እርሱ ተናግሯል (ዮሐ 10፡10)። ስለዚህ መንፈሳዊ ውጊያው የሚደረገው ከሰዎች ጋር ሳይሆን ነገር ግን ከኃላቸ በመሆን ማንነታቸውን በመቆጣጠር ከሚጠቀመው ከክፉ መንፈሳዊ ዓለም ጋር ነው (ኤፌ 6፡12)። የዓለምን አስተዳዳር፣ እውቀት፣ጥበብና ሀብት እንዳይጠቀም በመንፈስ መቃወም አስፈላጊ ነገር ነው።

**ኤፌ 6፡13 "ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም፥ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ" መቼ ነው ክፉ ቀን?** ማንኛውም ጊዜ ሊሆን ይችላል። እያንዳንዱ ሰከንድ የሚገጥመን ነገር ምን እንደሆነ አይታወቅምና የጌታ ዕቃ ጦር ያስፈልጋል። በርግጥ ሁሉም ክርስቲያን ማወቅ የሚገባው ሰይጣን እና ተከታዮቹ በጊዜ፣በቦታ፣ በእውቀትና፣ በዘላለማዊነትቱ ውስን (ፍጡር ነው)። ነገር ግን ውስጣዊ ጠላታችንን ማለትም ክፉውን የስጋ ፍላጎት እናም ውጫዊ ጠላታችንን ዓለምን ይጠቀማል።

**ኤፌ 6፡14-17 *ለመንፈሳዊ ውጊያ የሚጠቅሙ የእግዚአብሔር የጦር ዕቃዎች***

ስድስት ዓይነት መንፈሳዊ የጦር ዕቃዎች ተጠቅሷል። አንድ ጥሩ ትጥቅ የታጠቀ ወታደር ወደ አእምሮአችን እናምጣ። ሶስቱ የጦር ዕቃ ቁ.15 ላይ፣ አንዱ ቁ.16 እና ሁለቱ ቁ.17 ላይ ይገኛሉ። ተቃዋሚ ሰይጣን የብዙዎችን የእውቀት ባንክ እንደበከለና እንዳታለለም፤ በውሸትና በሸንገላ ሃሳብ የኤፌሶንንም አይሁድንና አህዛብን ሊያጠቃ እንደሚችል የሚያስረዳ ክፍል ነው።

**6፡15** *"እንግዲህ ወገባችሁን **<u>በእውነት ታጥቃችሁ፥</u>** **<u>የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፥</u>** **<u>በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት</u>** እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ"*

- **ኤፌ 6፡14 የእውነት ቀበቶ** (*መቀነት ወይም ዝናር*)፡- በወንጌል የተገኘውን እውነት ከመጽሐፍ ቅዱስ በማወቅ እንደቀበቶ ታጥቆ መዘጋጀትን ያሳያል። ቀብቶ (ዝናር) ሰይፍ መቀምጫ ቦታ ነው። ለውጊያም የመዘጋጀት አንዱ ሂደት ነው። አንድ ክርስቲያን እውነትን ማወቅ አለበት። እውነትን ማወቅ የሚችለው ደግሞ በእምነት ከጌታ ቃል ነው።

- **ኤፌ 6፡14 የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፡-** ይህ ደግሞ የመከላከልን ስዕላዊ መግለጫ ያሳያል። በተለይም ልብንና መተንፈሻ አካልን የሚከላከል መሳሪያ ነው።ታማኝነታችንና ክርስቲያናዊ ባህርያችን በጌታ የተገኘው ጽድቅ ዲያብሎስ ማየት አለበት (2ቆሮ 5፡21፣ኤፌ 4፡24)። ሰይጣን የክርስቶስን ጽድቅና የእኛንም የየቀኑ የጽድቅ ኑሮ ሲያይ ተሸናፊ እንደሆነ ያውቃል።

- **ኤፌ 6፡15 በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፡-**ጫማ ማድረግ ለመሄድ መዘጋጀት ነው። የሮማዊያን ወታደሮች መሬት የሚነክስ ጫማ ይጠቀሙ ነበር። ይህም መውደቅን ይከላከላል። የሰላምን ወንጌል ይዞ ለመሄድ ሁል ጊዜ ዝግጁዎች መሆን አለብን (ሮሜ 10፡15፣ኢሳ 52፡7)። ሰላም ደግሞ ለአይሁድም ሆነ ለአህዛብ ያስፈልጋል።

- **ኤፌ** 6፡16 **የእምነትን ጋሻ፡-** "በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን **የእምነትን ጋሻ** አንሡ"፡- በስሜት ላይ ያለተመሰረተ ህያው የሆነ እምነት ወይም ***በጌታ መታመን*** ወታደር ከጥቃት ራሱን የሚከላከልበት እንደ ጋሻ ምሳሌ ነው። በጌታ መታመን ከሠይጣን በየቀኑ ከሚልከው ፍላጻ ተከላካይ መሳሪያ ነው።ሰይጣን እንደ እሳት የሚንበለበል የሰውን ልብ የሚዋጋ ፍላጻ እንዳለ ማወቅ አለብን። ሁል ጊዜ እምነታችን የጸና መሆን አለበት።

- **ኤፌ** 6፡17 **የመዳንንም ራስ ቁር**፡- ካሳሻችን ሰይጣን የሔዋንን የእውቀት ማህደሯን አእምሮ (ራስ) በውሸት ሃሳብ እንዳጠቃት (ዘፍ 3 2ቆሮ 11፡1-3) የኤፌሶንንም አይሁድንና አህዛብን ሊያጠቃ እንደሚችል ይናገራል። መዳን እንደ ራስ ቁር ነው። ራስ እውቀት የሚያድግበት የሰውነት አካል ክፍል ነው። እውቀት ከተመታ የተሳሳተ ተግባር ያደርጋል። 2ጴጥ3፡18 "ነገር ግን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ"። በጌታ ቃል ማደግ አለብን። የድነት እውቀት እንደ ራስ ቁር ነው። የቃሉ እውቀት ከሌለን በተለያዩ የሐሰት ትምክቶች (የእኔ ዘር ይሻላል በማለት አይሁድንና አህዛብን በመለያየት) ወደ ጥፋት መሄድ ቀላል ነገር ይሆናል።

- **ኤፌ 6፡17 "የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው"፡-** ይህ መሳሪያ የማጥቂያ የጦር ዕቃ ነው። እንደየችግሩ ዓይነት የሚጠቅሙ የሰይፍ ዓይነቶች የተለያዩ ናቸው። ለአጭርና ለቅርብ ርቀቶች ይለያያሉ። የጌታ ቃል ውስጣችንንም የውጭ ጠላታችንንም (ክስና ሃሳብ) ያጠቃል። "የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም፥ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፥ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥ ምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፥ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል"

(ዕብ 4፡12)። ጌታ በሰይጣን ሲፈተን የተጠቀመው የእግዚአብሔርን ቃል ነበር (ሉቃ 4፡1-13)። ሰይጣን የጌታን ቃል ያለ ቦታ ለተንኮል እንደሚጠቀም መጠቀም የለብንም። ቃሉን ማንበብ ብቻ ሳይሆን ማሰላሰልና መተግበር አለብን። በዚያን ጊዜ እኔ አይሁድ ወይንም እኔ አህዛብ ነኝ አንባባልም።

**ኤፌ 6**፡18-20 ጸሎት፡-በኤፌሶን መልዕክት ጸሎት የታወቀ የህይወት ማዕከል ነው። ከዚህ በፊት ምዕራፍ 1 እና 3 ግልጽ የሆነ የጸሎት ጉዳዮች ቀርበዋል። ጸሎት ሚዛን ለጠበቀ መንፈሳዊ ህይወት አንዱ ክፍል ነው።

ምን ምን ጊዜና እንዴት እንጸልይ? አሁን ደግሞ እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች ሁሉ ከተናገረ በኋላ በህይወት ለማደግና አብሮ ለመቆየት ሁል ጊዜ በትጋት በመንፈስ መጸለይ መሰረታዊ ነገር ነው። በዚህ ክፍል ሶስት የጸሎት ርዕሶች ተጠቅሰዋል። 1. ለቅዱሳን 2.ወንጌልን በግልጽ ስለመናገር (አፉ በእግዚአብሔር ቃል እንዲከፈት) 3.ስለ ክርስቶስ በግልጽ ስለ መናገር ናቸው። ይህ ሁሉ በጌታ አንድ መሆኑን ከተረዳና ካመነ በኋላ ለሎችም በረከት መሆን ነው።

**ኤፌ**6፡21-22 በኤፌሶን ቤ/ክ እና በሐዋ ጳውሎስ መካከል ያገለግል ስለ ነበር ታማኝ ስለ ሆነው ስለ ቲክቆስ ይናገራል። ቲክቆስ ከኢስያ(ቱርክ) የተለወጠ ሰው ነው። በእስር ጊዜውም አብሮት ነበር። እርሱም 1. የተወደደ ወንድምና 2. በጌታ የታመነ አገልጋይ ነበር።

ኤፌ 6፡23-24 ባለው ክፍል ሐዋርያው በተለመደው የቡራኬ ሰላምታው መልእክቱን ሲደመድምም ሰላምና ፍቅር ከእምነት ጋር ለአማኞች እንዲሆን ይባርካል ስለ ጽናታቸውም ባለመጥፋት ከሚወዱ ሁሉ ጋር እንዲሆን ይመኛል።

## መደምደሚያ

የምንኖረው በሁለት ዓለም ነው ማለትም መንፈሳዊና አጥናፋዊ ዓለም። የማይታየው ብዙ ውጊያ ያለበት ነው። የሚታየውም ብዙ ፈተና ነው። ክፉውን የዚህን ዓለም ገዥ ለመቃወም መንፈሳዊ ዕውቀት ያሳያል። ጸሎትም መሰረታዊ ነገር ነው። ሐዋ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ አማኞች እንደሚከተለው ይላል "እኛ ግን ከቀን ስለ ሆንን፥ የእምነትንና የፍቅርን ጥሩር የመዳንንም ተስፋ እንደ ራስ ቁር እየለበስን በመጠን እንኑር" (1ተስ 5፡8)።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1) ኤፌ 6፡10 ካለፉት ምዕራፎች ሀሳብ ጋር ምን ይገናኛል?
2) ኤፌ 6፡11 ከውጊያው በፊት ልብስ መለበስ አለበት ይላል፡፤ ምን ዓይነት ልብስ ነው የሚናገረው?
3) ዲያብሎስ ማለት ምን ማለት ነው? ሰይጣንስ? ሥራው ምንድ ነው? (መሪው ያብራራላችሁ)
4) ኤፌ 6፡14-17 ሐዋ ጳውሎስ በምሳሌያዊ ንግግር የጠቀሳቸውን መንፈሳዊ የጦር ዕቃዎች በወታደር ትጥቅ ምሳሌ የተጠቀማቸው ስንት ናቸው? በሁሉም ተወያዩ።
5) ኤፌ 6፡18-20 ስለ ጸለያቸው ጸሎቶች ተነጋገሩ።

6) ዛሬ ስለመንፈሳዊ  ውጊያና ስለ ጸሎት ምን ተማራችሁ?

7) 2ቆሮ 10፥4-10 አንብባችሁ ላልዳኑ ሰዎች አሁን ጸልዩላቸው

8) ፈቃዳችሁ ከሆነ በሚቀጥለው ሳምንት ማዕድ በህብረት የሚትበሉበት ቀን ይሁን (ፍቅራችሁን፡ ለመግለጽ)። በዝግጅቱ ሁሉም ይሳተፍ። ጌታ ይባርካችሁ!